# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 037 ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# «የኢትዮ-ቻይና ግንኙነት ለቻይና አፍሪካ እና ለደቡብ-ደቡብ ትብብር ገንቢ ቅርጽ አስቀምጧል»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ለቻይና አፍሪካ እና ለደቡብ-ደቡብ ትብብር ገንቢ ቅርጽ ማስቀመጡን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቻይና ለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበልም ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቻይና ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ ከትናንት በስቲያ ቻይና ሲገቡ በቻይና ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ኪያንግ ደማቅ አቀባበል የተደረገላቸው ሲሆን በትናንትናው ዕለትም ከፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ ጋር በቻይና ታላቁ የሕዝብ አዳራሽ የሁለትዮሽ ውይይት አድርገዋል፡፡

"የኢትዮ-ቻይና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

ለክፍያ ብቻ አይደለም ...
አዋሽ ባንክ AwashBank
Awash E-School Management System




# በሽግግር ፍትህ

## መፍትሔ የማፈላለግ አስፈላጊነት ላይ ፅኑ እምነት ታይቷል

- **የመጀመሪያው የግብዓት ማሰባሰብ ምዕራፍ ተገባዷል**

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- እስካሁን ባካሄዳቸው ውይይቶች ሁሉም ተሳታፊዎች በሽግግር ፍትህ ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ መፍትሔ በማፈላለግ አስፈላጊነት ላይ ፅኑ እምነት

በሽግግር ፍትህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል ግንባታ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ይጠናቀቃል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ እንደሚጠናቀቅ የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ቢሮ የኮንትራት አስተዳደር ባለሙያ ወይዘሮ ፈትያ ነስሩ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የፕሮጀክቱ አብዛኛዎቹ የስትራክቸር ሥራዎች የተጠናቀቁ ሲሆን አጠቃላይ የግንባታው አፈጻጸም 55 ነጥብ 24 በመቶ ደርሷል።

የኮልፌ ጠቅላላ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# የቴሌቪዥን ድራማዎችና ተፅዕኖዎቻቸው

**መርድ ክፍሉ**

በሀገራችን በርካታ መገናኛ ብዙኃን እንደመኖራቸው በውስጣቸውም የተለያዩ ይዘት ያላቸው ፕሮግራሞች ይይዛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ድራማ ነው፡፡ በመገናኛ ብዙኃን በኩል የሚተላለፉ ድራማዎች በአብዛኛው ማኅበረሰቡ ላይ አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ እንደሚገኙ የሥነ ልቦናና የትያትር ጥበባት ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

የሥነ ልቦና ባለሙያ የሆኑት አቶ ብርሃኑ ራቦ እንደሚናገሩት፤ በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ድራማዎች ብዙ ተከታይ አላቸው፡፡ በተለይ በቤተሰብ ደረጃ ብዙ ተከታይ ስላላቸው በድራማዎቹ የሚተላለፉ መልዕክቶች በአዕምሮ የመቅረት ዕድላቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ ማንኛውም ድራማ አዝናንቶ የማስተማር ኃላፊነት አለበት፡፡ በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉት ድራማዎች ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ? ምንስ ትርጉም ይሰጣሉ? የሚለው በትኩረት መታየት አለበት፡፡

በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉት ድራማዎች በቤተሰብ

የቴሌቪዥን ድራማዎችና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ዜና



ሻለቃ መሃሪ ማሾ

# በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን አንድነትና ብዝሃነትን ማስተዋወቅ ላይ ከዚህ በተሻለ መሠራት አለበት

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን አንድነትና ብዝሃነትን ማስተዋወቅ ላይ ከዚህ በተሻለ መሠራት አለበት ሲሉ የቀድሞው የትግራይ ራስ ገዝ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ሻለቃ መሃሪ ማሾ ገለጹ።

የ84 ዓመቱ አዛውንት ሻለቃ መሃሪ ማሾ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን አሁን ካለችበት ችግር ለማውጣት አንድነትና ብዝሃነትን ማስተዋወቅ ላይ ከዚህ በተሻለ መሠራት አለበት። ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተፈጠረ ያለውን ችግር በመፍታት አንድነታቸውን አጠናክረው ለተሻለ ነገ ሊሠሩ ይገባል።

የቀድሞ አባቶች ጥልቅ የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸውና በራስ የመተማመን ኃይልን ተጎናጽፈው በብሔር፣ በሃይማኖት እና በአስተሳሰብ ልዩነት ቢኖራቸውም አንድ በመሆን አሁን ላይ ላለችዋ ኢትዮጵያ መሠረት ጥለው አልፈዋል ብለዋል።

እንደ ሻለቃ መሃሪ ገለጻ፤ የዜጎች የሕይወት መርህና አቅጣጫ የተለያየ ቢሆንም አወንታዊ እድገቶችን ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ተግዳሮቶች እና ዕድሎች የተቀላቀሉበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ ወጣቶች ንቁ እና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠት ወሳኝ ነው።

የመገናኛ ብዙኃን መብዛት ጋር ተያይዞ ብዛት ያላቸው መረጃዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚለቀቁ በመሆናቸው ያንን አገናዝቦ የሚያስፈልገውን በተግባር ላይ የማዋል ችግር ይታያል ያሉት ሻለቃ መሃሪ፤ ከሚሰጠው አወንታዊ አገልግሎት ባሻገር አሉታዊው እየበዛ በመምጣቱ ጉዳዩ አንድ ሊባልለት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሻለቃ መሃሪ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለያየ ቋንቋ ይናገር እንጂ ውስጡ አንድ ነው። በኢትዮጵያ 80 የሚጠጉ ብሔር ብሔረሰቦችና ቋንቋ ቢኖርም ኅብረተሰቡን አንድ የሚያደርገው በበጎነት እና በአብሮነት የመኖር እሴቶች ናቸው።

አሁን ያለው ትውልድ ከአባቶቹ የቀሰማቸውን መልካም ክዋኔዎች ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ የማቆየት ኃላፊነት አለበት ያሉት ሻለቃ መሃሪ፤ ወላጆች ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት ወቅት በሀገር ፍቅር ስሜት እና በኢትዮጵያዊነት ሥነምግባር ሊሆን እንደሚገባ አበክረው ገልጸዋል።

የትኛውም ሰው ሊገነዘበው የሚገባው ነገሮችን አርቆ ማየት እንዳለበት ነው፤ የቀድሞ አባቶች በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ለሀገራቸው ማድረግ የሚችሉትን አያሌ ተግባራት በማከናወን ኢትዮጵያን ማቆየት መቻላቸውን ያነሱት ሻለቃ መሃሪ፤ ከቀደመው ታሪካችን በጎውን በመውሰድ የተሻለች ኢትዮጵያ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ መወጣት ያለብንን ኃላፊነት ልንወጣ ይገባል ብለዋል።

አሁን ላይ ያለችው ኢትዮጵያ የቀድሞ አባቶች የሥራ ውጤት ናት፤ ታሪክ እየመዘዙ ግጭት መፍጠር ሳይሆን ታሪክ መሥራት እንደሚያስፈልግ ሁላችንም በመገንዘብ ለተተኪው ትውልድ የበለጸገች ሀገር ለማስተላለፍ በትምህርትና በሥራ በመዳበር ሁሉም በተሰማራበት የሥራ መስክ መትጋት አለበት ነው ያሉት።

# ምክር ቤቱ የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛ ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት አጸደቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ እና ደቡብ ኮሪያ እንዲሁም በኢትዮጵያ እና በሕንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛ ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት አጸደቀ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባውን ትናንት ሲያካሂድ፤ በኢትዮጵያ እና በደቡብ ኮሪያ እንዲሁም በሕንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛ ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት አጽድቋል።

ከደቡብ ኮሪያ ጋር የተደረገው ስምምነት አዋጅ ቁጥር 1305/2016 ሆኖ የጸደቀ ሲሆን ከሕንድ ሪፐብሊክ ጋር የተደረገው ስምምነትም አዋጅ ቁጥር 1306/2016 ሆኖ ጸድቋል።

በስምምነቱ መሠረት የዲፕሎማቲክ ወይም የሰርቪስ ፓስፖርት የያዙ የሁለቱ ሀገራት ዜጎች ለሥራ ጉዳይ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተሳለጠ እንዲሆን የሚያስችል መሆኑ ተገልጿል።

ቪዛ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ቅድመ-ሁኔታዎችና የሚወስደውን ጊዜ በማስቀረት የሚደረገው ጉዞ በቀላሉ እንዲመቻች ያደረጋልም ተብሏል።

ኢትዮጵያ ከደቡብ ኮሪያ እና ከሕንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት ጋር የሚኖራትን የሁለትዮሽ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር የሚያግዝ መሆኑም ተነስቷል።

ምክር ቤቱ በትናንት ውሎ በኢትዮጵያና በሊባኖስ መንግሥታት መካከል በሥራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅም መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ መርቷል።

በኢትዮጵያ እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥት መካከል በሁለትዮሽ ወታደራዊ ቴክኒካዊ ትብብር ወቅት የተገኙ የአዕምሯዊ የፈጠራ ሥራ ውጤቶች እና ንብረቶች የጋራ ጥበቃ ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅም መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

የአፍሪካ መድኃኒቶች ኤጀንሲን ማቋቋሚያ ስምምነትም ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

በኢትዮጵያ እና በፓኪስታን እስላማዊ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተፈረመውን የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነትም በተመሳሳይ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል ሲል የዘገበው ኢዜአ ነው።

# በክልሉ የሚገኙ 42 ወረዳዎች ከትራኮማ በሽታ ነፃ ሆነዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በክልሉ የሚገኙ 42 ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ ከትራኮማ በሽታ ነፃ መሆናቸውን የአማራ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች 43 ሺህ ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው ተገልጿል፡፡

በአማራ ክልል ጤና ቢሮ የትራኮማ ፕሮግራም ቴክኒካል አማካሪ አቶ ስንታየሁ አወቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓለም ጤና ድርጅት የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት 42 ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ ከትራኮማ በሽታ ነፃ ሆነዋል።

የትራኮማ በሽታን በመከላከልና በማከም ረገድ ለረጅም ዓመታት በርካታ ሥራዎች በመከናወናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ መጥተዋል ሲሉም አማካሪው ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ በክልሉ በሚገኙ 59 ወረዳዎች ትራኮማ በሽታን ማጥፋት የሚያስችል ሰፊ ዘመቻ ተከናውኗል ያሉት አቶ ስንታየሁ፤ ከዚህ ቀደም በነበሩ ጊዜያት በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች በሚባል መልኩ የትራኮማ ተጠቂዎች እንደነበሩ አስታውሰዋል፤ አሁን ችግሩ እየቀነሰ መሆኑንም አመላክተዋል።

እንደ አቶ ስንታየሁ ገለጻ፤ ከዓይን ቆብ መቀልበስ ጋር ተያይዞ ለዓይነ ስውርነት የሚያጋልጠውን የትራኮማ በሽታን የመከላከልና የማከም ሥራ በክልሉ በስፋት እየተከናወነ ይገኛል።

አሁን ላይም ቢሆን በሽታውን ለመከላከል በተለያዩ ወረዳዎች ላይ የመድኃኒት ዕደላና የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

አሁን ላይ በክልሉ የሚገኙ 43 ሺህ ዜጎች የትራኮማ በሽታን መከላከል የሚያስችል የዓይን ቀዶ ጥገና ሕክምና ያስፈልጋቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ቀደም ካሉ ዓመታት አንጻር ሲታይ አገልግሎቱ በስፋት እየተሰጠ በመሆኑ የታካሚዎች ቁጥር ካለፉ አመታት ጋር ሲነጻጸር መቀነሱንም ነው አቶ ስንታየሁ ያመላከቱት፡፡

በዘንድሮው በጀት ዓመት ከመድኃኒት አቅርቦት ጎን ለጎን ለ43ሺህ ዜጎች አገልግሎቱን ለመስጠት መታቀዱንም አስታውቀዋል።


ከሠላምና ደህንነት ጋር በተያያዘ በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ችግሮች እንደነበሩ ጠቁመው፤ ሠላማዊ በነበሩ አካባቢዎች ላይ በሽታውን የመከላከል ሥራዎች ተሠርተዋል፤ የጸጥታ ስጋት በነበረባቸው ቦታዎች ጭምር የመድኃኒት አቅርቦት እንዲስፋፋ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በሽታውን የመከላከል ሥራው ቤት ለቤት የሚከናወን በመሆኑ ሠላምና ደህንነት ካልተረጋገጠ ሥራዎችን መሥራት አዳጋች እንደሚሆን ተናግረው፤ ይህ የበሽታው መከላከል ላይ ስጋት መፍጠሩን ጠቁመዋል።

በሽታውን ለመከላከልም የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የግል ንጽህናን መጠበቅና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች በስፋት እንደሚከናወኑ አቶ ስንታየሁ ገልጸዋል።

በሽታው ሲከሰትም የከፋ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ለበርካታ ዜጎች መድኃኒት የማዳረስ ሥራና አስፈላጊውን የሕክምና ድጋፍ ለመስጠት ባለሙያዎች ዝግጁ ሆነው እየጠበቁ መሆኑን አመላክተዋል።

# የተመድ አማካሪ ያወጡት መግለጫ ኃላፊነት የጎደለውና ተገቢ ጥናት ያልተካሄደበት ነው



**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል መከላከል ልዩ አማካሪ የሆኑት አሊስ ዋይሪሙ ኢትዮጵያን በተመለከተ ያወጡት መግለጫ ኃላፊነት የጎደለውና ተገቢ ጥናት ያልተካሄደበት መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ባለፈው ሐሙስ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አማካሪ ከሰሞኑን በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ መስከረም 29 እና 30 ሁለት መግለጫዎችን አውጥቷል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል መከላከል ልዩ አማካሪ የሆኑት አሊስ ዋይሪሙ ኢትዮጵያን በተመለከተ ያወጡት መግለጫ ኃላፊነት የጎደለውና ኢትዮጵያን የማይገልጽ ነው ብለዋል፡፡

ኃላፊዋ ያወጡት መግለጫ ኃላፊነት የጎደለው፣ ተገቢ ጥናት ያልተካሄደበትና መሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ የማይገልጽ ነው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል ብለዋል፡፡

በፕሪቶሪያ የሠላም ስምምነት ለአፍሪካውያን ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ በሚል የሰሜኑ ጦርነት መፍትሔ ማግኘቱንም አስታውሰዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ከሽግግር ሥርዓቱ ጋር በተያያዘና ከብሔራዊ መግባባት ጥረቱ ጋር ያሉ ነገሮችን ተገቢውን መረጃ ያልወሰደ ነው፡፡ የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል የተቋቋመውና አሁን ጊዜው ያበቃውን ኮሚሽንን ጠቅሶ ያወጣው መግለጫ ውሃ የማይቋጥር ነው፡፡ እንዲሁም ኃላፊነት የጎደለው፣ ተገቢ መረጃ የሌለውና በተገቢው ሁኔታ ያልተነተነ መግለጫ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአማካሪዋን መግለጫ ተገቢ አለመሆኑን በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በቦታው ላይ ተገኝቶ በመረጃ ያልተደገፈና ከትክክለኛ የመረጃ ምንጭ መረጃ ሳይጠቀም ያወጣው ሪፖርት ኃላፊነት የጎደለው በመሆኑ ኢትዮጵያ አትቀበለውም፡፡

ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ በተከሰቱ ግጭቶች ያለውን ወቅታዊ የሰብዓዊ ሁኔታ በተመለከተ ኢትዮጵያ አትቀበለውም ያለው መግለጫው፤ የኮሚሽኑ ትክክለኛ የምርመራ ሂደትን ያልተከተለና በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ መሬት ላይ ያለውን እውነታ ያላገናዘበ ነው፡፡

በሰሜኑ ክፍል የተከሰተውን ጦርነት ለማስቆም ባለፈው ዓመት በደቡብ አፍሪካ የፕሪቶሪያ ስምምነት መፈረሙን ያስታወሰው መግለጫው በሰሜን የሀገሪቱ ክፍል የጥይት ድምፅ እንዳይሰማ ማድረግ መቻሉንም አንስቷል፡፡




ፎቶ፡ አዩብ ተፈራ

# የአፍሪካ የእንስሳት ዕርባታ ዓውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ከ17 ሀገሮችና ከ100 በላይ ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂና ግብዓት አቅራቢዎች እንዲሁም የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት ስምንተኛው የአፍሪካ የእንስሳት ዕርባታ ዓውደ ርዕይ በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ ተገለጸ።

በስምንተኛው የአፍሪካ የእንስሳት ዕርባታ ዓውደ ርዕይ እና 12ኛው ኢትዮ የዶሮ እርባታ ኤክስፖም በእንስሳት መኖ፣ በእንስሳት ጤና፣ በዶሮ እርባታ፣ በወተት፣ በስጋ እንዲሁም በንብ እና በዓሣ ሀብት ልማት ዘርፎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ተገልጿል። የገበያ ሰንሰለቶች ላይ ያሉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለማስተዋወቅ እንደሚረዳም ተመላክቷል።

በግብርና ሚኒስቴር የዘርፉ ባለሙያ አቶ አዋሳ ጻላ እንደገለጹት፣ ዓውደ-ርዕዩ ለወተትና ስጋ ዘርፎች ዕድገትና ልማት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው። ልምድና ተሞክሮ ለማጋራትና የአቻ ለአቻ የንግድ ትስስር መርሐ-ግብሮችን በማዘጋጀት ረገድ የላቀ ሚና ይኖረዋል። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅና የእውቀት ሽግግርን ለመፍጠር ያስችላል።

በተለይም በእንስሳት ሀብት ልማት ምርታማነትን በማሳደግ ተጨማሪ ሀገራዊ የኢኮኖሚ አቅም ለመፍጠር አስቻይ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ያሉት አቶ አዋሳ፤ ለዚህም ግብርና ሚኒስቴር የማስተባበር ሚናውን እንደሚወጣ ተናግረዋል።

የኤክስፖው ቡድን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አሳማ ሙስጠፋ፤ ከዚህ በፊት በነበሩት መርሐ-ግብሮች ዓውደ-ርዕዩ ትልቅ ስኬት በማስመዝገብ የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ በዘርፉ ተዋንያን መካከል ለመቀራረብ ምቹ መድረክ መሆን እንደቻለ አስታውቀዋል።

በዘንድሮው መርሐ - ግብር ከ17 ሀገራት የተውጣጡ ከ100 በላይ ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂና ግብዓት አቅራቢዎች እንዲሁም የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች እንደሚሳተፉ ጠቅሰዋል።

የፕራና ኤቨንት ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ነቢዩ ለማ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ያላትን የእንስሳት ሀብት በማሳደግ የምግብ ዋስትናዋን እንድታረጋግጥ ሁነቱ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን ተናግረዋል።

ዓውደ-ርዕዩ በፕራና ኢቨንትስና ግብርና ሚኒስቴርን ጨምሮ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር ከጥቅምት 15 እስከ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ እንደሚዘጋጅ ጠቅሰው፣ ከአራት ሺህ በላይ የንግድ ጎብኚዎች እንደሚስተናገዱበት አስታውቀዋል።

ለሦስት ቀናት በሚካሄደው ዓውደ ርዕይ የእሴት ሰንሰለቱን የሚወክሉ መሠረታቸውን ካናዳ፣ ቻይና፣ ኢትዮጵያ፣ ግብጽ፣ ጀርመን፣ ሃንጋሪ፣ ሕንድ፣ ኬንያ፣ ጆርዳን፣ ሊባኖስ፣ ኔዘርላንድ፣ ስኮትላንድ፣ ስፔን፣ ቱርክ፣ ዩክሬን፣ እንግሊዝና አሜሪካ ያደረጉ ዓለም አቀፍ የዘርፉ መሪዎችና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ከንግድ ጎብኚዎች ጋር እንደሚገናኙ ተጠቅሷል።


እንደ አዘጋጆቹ ገለጻ፤ የ2016ቱ ዓውደ ርዕይ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከ50 በመቶ በላይ የተሳታፊዎችና የጎብኚዎች እድገት ያሳያል።

# የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚና በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አምባሳደር ተፈራ ደርበው



ቢልለኔ ስዩም

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያና ቻይና ግንኙነት በዲፕሎማሲ እና ኢኮኖሚው መስክ እንዲሁም በሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ረገድ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ እንደሚገኝ በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈራ ደርበው ተናገሩ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ቻይና ቤጂንግ መግባታቸው ይታወቃል።

በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈራ ደርበው እንደገለጹት፣ የቻይናና የኢትዮጵያ ግንኙነት ባለፉት 30 አመታት በላቀ ሁኔታ አድጓል።

ቻይናና ኢትዮጵያ በሁለትዮሽ፣ በቀጣናዊና በባለ ብዙ መድረክ ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ አቋም በማራመድ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እንዲሰፍን በጋራ እንደሚሠሩ ነው አምባሳደር ተፈራ ያመለከቱት።

ኢትዮጵያና ቻይና በዲፕሎማሲ እና ኢኮኖሚው መስክ በተለይም በኢንቨስትመንት፣ በንግድና ቱሪዝም ዘርፍ ያላቸው ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መጥቷል ያሉት አምባሳደር ተፈራ፤በሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ረገድም ጠንካራ ግንኙነት እንዳላቸው አውስተዋል።

በርካታ ኢትዮጵያውያን በትምህርት ዕድልና በሌሎች መስኮች ወደ ቻይና መጥተው ተጠቃሚ መሆናቸው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ እንዲጠናከር ማስቻሉን ነው ያብራሩት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በቻይና እያደረጉ ያሉት የሥራ ጉብኝትም የሁለቱን ሀገራት የረጅም ዘመናት ግንኙነት ጥልቀት እንዲኖረውና ወደ ላቀ ደረጃ የሚያደርስ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተያያዘም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከቻይናው ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ኪያንግ ጋር ያደረጉት ምክክር ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ጠንካራ የሁለትዮሽ ግንኙነት ይበልጥ ለማሳደግ ያላትን ፍላጎት ያሳየችበት መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ቢልለኔ ስዩም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እና የልዑክ ቡድናቸው በቻይና እያደረጉ የሚገኙትን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት አስመልክቶ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ቢልለኔ ስዩም በሰጡት ማብራሪያ፣ የቻይናው ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ኪያንግ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ይፋዊ አቀባበል ማድረጋቸውንና የአቀባበል ሥነ ሥርዓቱ የሁለቱን ሀገራት ጠንካራ ግንኙነት በሚያመላክት መልኩ መከናወኑን ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ኪያንግ ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የሁለትዮሽ ግንኙነት ለዘመናት የዘለቀ ጠንካራ መሆኑን መግለጻቸውንና አሁንም የበለጠ ከፍ ለማድረግ ፍላጎት መኖሩን መጥቀሳቸውን አመላክተዋል።

በውይይታቸው ወቅትም መሪዎቹ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የምጣኔ ሀብት ትብብር ግንኙነት ማጠናከሪያ መንገዶችን ማንሳታቸውንም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በቀጣናውና በኢትዮጵያ ሠላም እንዲሰፍን ያከናወኑትን ዘርፈ ብዙ ተግባር ማድነቃቸውንም ነው የተናገሩት።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት እየተተገበረ የሚገኘውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብርም ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን እንደጠቀሱና ቻይና አሁን ያለውን የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት በተለያዩ መስኮች በላቀ ሁኔታ የማሳደግ ሰፊ ፍላጎት እንዳላት ማስታወቃቸውን ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በበኩላቸው በኢትዮጵያ መንግሥት የተወጠኑ ባለብዙ ዘርፍ የእድገት ዓላማ ብሎም የተገኙ ድሎችን መግለጻቸውን ኃላፊዋ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላትን የንግድ ግንኙነት የማስፋፋት አስፈላጊነትን አፅንዖት ሰጥተው ማንሳታቸውን ገልጸዋል።

ከውይይቱ በኋላም ሁለቱ መሪዎች በተገኙበት በሀገራቱ መካከል አስራአራት የሚሆኑ የተለያዩ የመግባቢያ ስምምነቶች መፈረማቸውንም አብራርተዋል።

# በሽግግር ፍትህ መፍትሔ የማፈላለግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዳለ ማረጋገጥ መቻሉን የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮች ላይ ሲደረጉ የቆዩ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች መጠናቀቃቸውን አስመልክቶ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡

እንደ ሽግግር ፍትህ ባለ ግዙፍ ሀገራዊ አጀንዳ የማይመሳሰሉ አመለካከቶች ሊንፀባረቁ የሚችሉ መሆኑ የሚጠበቅ ጉዳይ መሆኑን የጠቆመው መግለጫው፤ በምክክር ሂደቱ አሉታዊ አመለካከትን ያንፀባረቁ በጣት የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች እንደነበሩ አመልክቷል፡፡

ጥቂት ተሳታፊዎች በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የቀጠለው ግጭትና የፀጥታ ሁኔታ ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ እንቅፋት ሊፈጥር እንደሚችል ስጋታቸውን መግለጻቸውን ነው የጠቆመው፡፡

ሌሎች ውስን ተሳታፊዎችም በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን በማንሳት ስጋታቸውን መግለፃቸውን ጠቅሷል።

በአሁኑ ጊዜ የግብአት ማሰባሰቡ ሂደት የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ደርሷል ያለው መግለጫው፤ በቀጣይ ምዕራፍ የሪፖርትና የፖሊሲ ረቂቅ ዝግጅትን የሚመለከት ሥራ ይሠራል፤ ሪፖርቱ አጠቃላይ የምክክር ሥራዎቹን ሂደት ይዳስሳል ብሏል፡፡

የተሰበሰቡ ግብአቶችን ዓለምአቀፋዊ ደረጃን በጠበቀ መንገድ በማጠናቀር እና በመተንተንም ዋና ዋና ግኝቶችን፣ ድምዳሜዎችን እና የሽግግር ፍትህ ዋና ዋና አላባዎችን በማካተት እንደሚደራጅም ነው የጠቀሰው፡፡

ይህ ማለትም የክስ እውነትን የማፈላለግ፣ የእርቅ፣ የምህረት፣ የማካካሻ፣ የተቋማዊ ማሻሻያ፣ የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን እና የባህላዊ አደረጃጀቶች እና የክልሎች ሚና ምንነትን በመዘርዘር እንዲሁም የቀረቡ ምክረ ሃሳቦችን በማካተት እንደሚደራጅ ገልጿል፡፡

ቀጥሎም በሪፖርቱ ግኝቶች ላይ የተመሠረተ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ረቂቅ የሚዘጋጅ ይሆናል ብሏል።

ሪፖርቱም ሆነ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነዱ ለሕዝብ በይፋ እንደሚቀርብና ፖሊሲው በኅዳር 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በሚደረጉ ተጨማሪ የድህረ ፖሊሲ ውይይቶች ዳብሮ የመጨረሻ መልኩን እንደሚይዝም በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡

በእያንዳንዱ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረክ ላይ 60 በጥንቃቄ የተመረጡ ተሳታፊዎች የተጋበዙ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች መገኘታቸው ከፍተኛ እምነት ያሳደረ መሆኑን ያሳየ አጋጣሚ ሆኖ ማለፉን መግለጫው ጠቁሟል፡፡

ከከተሞች እና አጎራባች አካባቢዎች የተወከሉ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባዎች በግብአት ማሰባሰብ መድረኮቹ ቀዳሚ ትኩረት እንደተሰጣቸው አመልክቷል፡፡

በእያንዳንዱ መድረክ ከተጋበዙ ተሳታፊዎች እስከ 60 በመቶ የሚደርሱት ሰዎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች መሆናቸውንና አቋማቸውን በነፃነት እንዲያንጸባርቁ አስቻይ ዕድል መፈጠሩም ተጠቅሷል።

በእስካሁኑ ሂደት የባለሙያዎች ቡድኑ 47 ክልላዊ እና ስምንት ሀገር አቀፍ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች መካሄዳቸውን፣ በ12 ክልሎችና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች በልዩ ሁኔታ በተለዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ ዘጠኝ የግብአት ማሰባሰቢያ ሕዝባዊ ውይይቶችንም ማካሄዱን አስታውሷል፡፡

ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሰዎችን በማወያየትና በርካታ ግብአቶችን በማሰባሰብ የመጀመሪያና ወሳኝ የግብአት ማሰባሰብ ምዕራፍ መገባደዱንም አመልክቷል፡፡ በፀጥታ ችግር ምክንያትም አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፉ ማድረጉንም ጠቁሟል፡፡

የምክክር ሂደቶቹ በኢትዮጵያ ያለውን ልዩ ብዝሃነት ግምት ውስጥ በማስገባት መከናወኑም ተጠቁሟል፡፡

በምክክሮቹ የሴቶችን ተሳትፎ የበለጠ ለማጎልበት መሠራቱን፣ ከተደራሽነት አንፃርም በሁሉም መድረኮች የተካሄዱ ውይይቶች በሽግግር ፍትህ ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖር መቻሉንና በቋንቋ አጠቃቀምም ተሳታፊዎች በውይይቶቹ ላይ ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ዕድል መስጠቱም ተጠቁሟል፡፡

የውይይት መድረኮቹ የሚመሩባቸው ደጋፊ ሰነዶች በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛ እና በሶማሊኛ ቋንቋ አስቀድሞ መተርጎማቸው ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን አስተዋፅኦ አድርጓልም ተብሏል።

# «የኢትዮ-ቻይና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ እንደገለጹት፤ የኢትዮ- ቻይና ግንኙነት ለቻይና አፍሪካ እና ለደቡብ- ደቡብ ትብብር ገንቢ ቅርጽ ያስቀመጠ ሲሆን በቀጣዩ ዘመን ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ተግዳሮቶች፣ እስካሁን የተገባውን ትብብር ይበልጥ ማጠናከር ይሻል።

የቻይና ኢንቨስትመንት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እመርታ የሚኖረውን አስተዋፅዖ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)፤ በተለይም በአምስቱ ቁልፍ ምሰሶዎች፤ ማለትም በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በአይሲቲ፣ በማዕድን ልማት እና በቱሪዝም ተጨማሪ ኢንቨስትመንት እንዲኖር የማበረታቻ ጥሪ አቅርበዋል።

«ቻይና የኢትዮጵያ ቁልፍ አጋር ሆና ቀጥላለች» ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ «ለተደረገልን ደማቅ አቀባበል እና ላካሄድነው ፍሬያማ ውይይት ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግን እናመሰግናለን» ብለዋል፡፡

በሁለትዮሽ ውይይቱ ወቅት ፕሬዚዳንት ሺ በኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀል ሁነት ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንኳን ደስ ያለዎት ብለዋቸዋል።

የኢትዮጵያ እና ቻይና ግንኙነትም ከሁሉን አቀፍ ፅኑ ግንኙነት ወደ ሁኔታ የማይፈታው ስልታዊ ትብብር እና ወዳጅነት ደረጃ ከፍ ማለቱን በይፋ አብስረዋል።

የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብርን ያደነቁት ፕሬዚዳንት ሺ፤ ከቻይናው አረንጓዴ ልማት ፖሊሲ ጋር ተናባቢ በመሆኑ የግሪን ቤልት እና ሮድ አካል ሆኖ ሊደገፍ እንደሚችል አረጋግጠዋል።

# የቴሌቪዥን ድራማዎችና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ደረጃ የሚታዩ እንደመሆናቸው የሥነልቦና አጠባበቅ፣ ሃይማኖታዊ ንግግር እንዲሁም ሌሎች ንግግሮች ትርጉማቸው ቀደም ብሎ መታየት አለበት:: ድራማዎቹን የሚሠሩት አካላት ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ካተኮሩ ግን ድራማው ትርጉም አልባ እንደሚሆን ይናገራሉ:: ማኅበረሰቡን የሚያስተምሩ ሥራዎች ለመሥራት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ይጠቅሳሉ::

ለምሳሌ በኢ.ቢ.ኤስ ቴሌቪዥን (EBS) የሚተላፈውን ‹‹በስንቱ›› ድራማ ያነሱት አቶ ብርሃኑ፤ በድራማው ላይ የሚተውነው ሕፃን ልጅ የሚናገራቸው ነገሮች በቀላሉ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑን ይጠቅሳሉ:: ገፀ ባህሪውን የወከለው ልጅ ትምህርት ምንም እንደማያስፈልግና እንደማይጠቅም የሚናገርበት ሁኔታ ልጆች ጭንቅላት ላይ ከተቀመጠ በትምህርት ላይ የሚኖረው መተማመንን እንዲቀንስ እንደሚያደርግ ያስረዳሉ::

መገናኛ ብዙኃን የሚያስተላልፉትን ድራማዎች ይዘት በአግባቡ መገምገም ካልቻሉ ኅብረተሰቡን ከማስተማር ወደ ማደናገር እንደሚወስዱ ያብራሩት አቶ ብርሃኑ፤ በተጨማሪም ሀገርን ወደ ውድቀት የሚወስድ ትውልድ ሊፈጥር ስለሚችል መፍትሔ ሊበጅለትና የሚተላለፉ ድራማዎች ማኅበረሰቡ ላይ ምን ተፅዕኖ አላቸው የሚለው በአግባቡ መታየት እንዳለበት ያመላክታሉ::

እንደ አቶ ብርሃኑ አባባል፤ ሕግን የሚጥሱ አባባሎችና መልዕክቶች እንዲሁም ማኅበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩት በሕግ አግባብ የሚጠየቁበት ሁኔታ መፈጠር አለበት:: በሌሎች ሀገራት መገናኛ ብዙኃን ድራማዎችን በየትኛው ሰዓት ማስተላለፍ እንዳለባቸው ሕግ አስቀምጠዋል:: እኛ ሀገር ግን እንደዚያ አይታይም:: ድራማዎች በሁሉም ሰዓት ሲተላለፉ ይስተዋላል::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ቤት መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ የቴሌቪዥን ታሪክን ስንለመከት ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ብቻ የነበረው ድራማ የማስተላለፍ ሥራ በአሁን ወቅት ተስፋፍቶ በግልም መገናኛ ብዙኃን ተከታታይና አጫጭር ድራማዎች እየታዩ እንደሚገኙ ይገልፃሉ:: አብዛኛዎቹ ድራማዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴን የሚያሳዩ ሲሆን ወጣቱና ሕፃናቱ በድራማዎቹ እየተዝናኑ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠቅሳሉ::

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ገለፃ፤ በመገናኛ ብዙኃን በሚተላለፉ ድራማዎች የማኅበረሰቡን አስተሳሰብ የመቅረፅ ኃይል አላቸው:: ድራማዎቹ በመልካም መንገድ ከተሠሩ መልካም ነገርን በመጥፎ መልኩ ከተቀረፁ ደግሞ መጥፎ አስተሳሰብን ይዘራሉ:: ለአብነት በተደጋጋሚ በሚሠሩ ድራማዎች ላይ ገፀ ባህሪው ሲናደድ መጠጥ ሲጠጣ ወይም ሲጋራ ሲያጨስ ይስተዋላል:: ይህ ነገር በማኅበረሰቡ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ አለ::

‹‹በድራማዎች ላይ የሚስተዋሉ የሴቶች አለባበስ ማኅበረሰቡ ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ መታየት አለበት›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ፤ በተለይ ሕፃናት በድራማዎች ላይ የሚያዩት አለባበስ በሥነልቦናቸው ላይ ተፅዕኖ እንደሚመጣ ያስረዳሉ:: በሌላ በኩል በድራማዎች የሚታዩት ፀብ፣ መናናቅ እና አለመከባበር ሕፃናት ላይ የተሳሳተ አስተሳሰብ እንዲፈጠር ሊያደርግ እንደሚችል በመጥቀስ፤ በዚህም ሕፃናቱ በሚያድጉበት ወቅት ኃላፊነት ቦታ ላይ ቢቀመጡ ተጨቃጫቂ እንዲሁም ልዩነት ላይ የሚያተኩሩ እንዲሆኑ እንደሚያርጋቸው ያብራራሉ::

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ገለፃ፤ ብዙዎቹ ሲትኮም ተብለው የሚሠሩ ድራማዎች ችግርን ነቅሶ ከማውጣት ጀምሮ እንከን አለባቸው:: ደራሲዎቹ ሥራውን ከመሥራታቸው በፊት ጥናት ስለማያደርጉ የመሰላቸው ነገር ላይ ሲሠሩ ይስተዋላል:: በዚህም ውጤታቸው ዝቅተኛ ነው:: ሥራውን የሚሠሩት ሰዎች በርዕስ አመራረጥ፣ የአቀራረብ ሁኔታ እንዲሁም በሌሎች ከኅብረተሰቡ መብለጥ አለባቸው::

በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደሴ ከፍአለ፤ በመገናኛ ብዙኃን ላይ የሚተላለፉ ማንኛውም ይዘት ያላቸው ሥራዎች የራሳቸው የመገናኛ ብዙኃኑ መሆኑን ይናገራሉ:: ባለሥልጣኑ በመገናኛ ብዙኃኑ የሚተላለፉትን ሞኒተር በማድረግ ቁጥጥር ሲያደርግ የመገናኛ ብዙኃን አዋጅ፣ የማስታወቂያ አዋጅ እንዲሁም የሙያ ሥነምግባር ላይ ያተኮረ አዋጅን መሠረት አድርጎ መሆኑን ይጠቁማሉ:: በመገናኛ ብዙኃኑ ላይ በሚስተዋሉ ግድፈቶች ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ግብረመልስ እንደሚሰጥ ይናገራሉ::

እንደ አቶ ደሴ ገለፃ፤ ሌላው በመገናኛ ብዙኃኑ ላይ በሚቀርቡ ቅሬታና ጥቆማ መሠረት ቁጥጥር ይደረጋል:: ለምሳሌ አንድ ሰው በመገናኛ ብዙኃኑ እየተላለፈ ያለው ድራማም ሆነ ሙዚቃ ከማኅበረሰብ አንፃር ችግር የሚፈጥር ነው፤ ከሕግም አንፃር ችግር ያመጣል ብሎ ጥቆማ ሊሰጥ ይችላል:: ጥቆማውን መሠረት አድርጎ ምርመራ ተደርጎ ግብረ መልስ ይሰጣል:: የተገኘው ግድፈት ከፍተኛ ከሆነ ወደ ቅጣት ሊኬድ ይችላል:: አጠቃላይ በመገናኛ ብዙኃን በኩል የሚተላለፉትን ሁሉንም ይዘት መከታተል ቢከብድም በሚደርሱ ጥቆማዎች መሠረት ክትትል ይደረጋል::

# የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል ግንባታ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል የከተማ አስተዳደሩ ትኩረት ሰጥቶ ከሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች አንዱ መሆኑን የጠቀሱት ወይዘሮ ፈትያ፤ በከተማዋ የጤና አገልግሎት ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች በመሄድ አገልግሎቱን ለማግኘት ሲገደድ ቆይቷል ብለዋል። ስለሆነም ኅብረተሰቡ የሆስፒታሉን መጠናቀቅ በጉጉት እየተጠባበቀ እንደሚገኝ ነው ያመለከቱት።

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ቤቴል አካባቢ የሚገነባው ኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል መንግሥታዊ በሆነው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢኮስኮ) የግንባታ ሥራ ተቋራጭነት እየተካሄደ መሆኑን የኮንትራት አስተዳደር ባለሙያዋ ጠቅሰው፣ ተቋራጩ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የሚገነባውን ሆስፒታል ጨምሮ ሌሎች ሰፊ ሀገር አቀፍ መሠረተ ልማቶችን እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ሆስፒታሉ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የአካባቢው ማኅበረሰብ የጤና አገልግሎት ለማግኘት የሚደርስበትን እንግልት ያቃልላል የሚል እምነት እንደተጣለበትም ይገልጻሉ።

ሆስፒታሉ በ33 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 11 ሺ 300 ካሬ ሜትሩ ሕንፃዎች ያረፉበት ቦታ ነው። አጠቃላይ በጀቱም ከሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ነው።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሆስፒታሉ ግንባታ ከ70 በላይ ቋሚና ከ500 ጊዜያዊ የሥራ ዕድልም ፈጥሯል፡፡

ግንባታው ለሆስፒታል አስፈላጊ የሆኑ እንደ ጋራዥ፣ መጋዘን፣ የተሟላ የመኪና መቆሚያ፣ የውሃ እና የመብራት አገልግሎት መስጫ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ፣ የተሟላ መታጠቢያና መጸዳጃ ቤት፣ የኤክስ-ሬይ(x-ray)፣ እና ለሕክምና አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች ይኖሩታል።

የኮልፌ ቀራንዮ ጠቅላላ ሆስፒታል የሎት አንድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር በእውቀት መራ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ የሆስፒታሉ ግንባታ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2 ቀን 2021 የተጀመረ ሲሆን በተያዘው 2016 በጀት አመት ለማጠናቀቅ እየተሠራ ይገኛል።

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ቋሚ የሆነ 423 ታካሚዎችን የሚያገለግል አልጋዎች የሚይዝ ሲሆን በአንድ ጊዜም ከ500 በላይ የሚሆኑ ፅኑ ህሙማንን ማስተናገድ የሚያስችል አቅም ያለው ነው።

ኢንጂነር በእውቀት እንዳብራሩት፤ የሆስፒታሉ ግንባታ ፕሮጀክቱ 14 ሕንፃዎች ያሉት ሲሆን፣ ግንባታውን የሚያከናውነው ተቋራጭ ፕሮጀክቱን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ በሁለት ሎት እና በሁለት ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ እየሠራ መሆኑ ታውቋል።

ግንባታው በግንባታ ቴክኖሎጂዎች በተዘጋጀ የአርማታ ሙሌት የሚከናወን በመሆኑ የኮንክሪት ሙሌት ሳይት ላይ የሚዘጋጅ ሳይሆን ተዘጋጅቶ በሚቀርብ አርማታ በፓምፕ የሚሞላ ነው።

የሆስፒታሉ ግንባታ የአእምሮ ህክምና፣ የእናቶች እና የሕፃናት ህክምና፣ የካንሰር ህክምና መስጫ እና ማዋለጃ፣ የድንገተኛ ክፍል፣ ላብራቶሪ፣ አክስ-ሬይ /X-ray/፣ የጨረር ህክምና (Nuclear medicine)፣ የሥነ- ልቦና ህክምና መስጫ፣ የቀዶ ጥገና ህክምና መስጫ፣ ማቀዝቀዣ ክፍል፣ ቤተመጻሕፍት፣ ካፍቴሪያ እና መሰብሰቢያ አዳራሽ የያዘ ነው።

የአእምሮ ህሙማን፣ የእናቶች እና ሕፃናት፣ የኤክስ- ሬይ እና የተለያዩ ምርመራዎች እንዲሁም የካንሰር ህክምናን ጨምሮ ኅብረተሰቡ የተቸገረባቸውንና ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳረግባቸውን ህክምናዎች አቅፎ የሚይዝ ሆስፒታል እንዲሆን ተደርጎ እየተገነባ እንደሆነም ኢንጂነር በእውቀት ገልጸዋል።

የግንባታ ሂደቱ እንደተጀመረ በቁፋሮ ሂደቱ ላይ ባጋጠመው ጠንካራ አለት እንዲሁም በአንዳንድ የዲዛይን ጉዳዮች የተወሰነ መዘግየት መታየቱን ጠቅሰው፣ አሁን ግንባታው በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለኮሚሽኑ ተልዕኮ ስኬት ዜጎች ለአካባቢያዊና ሀገራዊ ሰላም ተግተው ሊሠሩ ይገባል!

በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉት አለመግባባቶች እና ግጭቶች በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብሎ ካለመነጋገር የመነጩ ናቸው። በተለይም በፖለቲከኞች እና በልሒቃን መካከል ያለው አለመተማመን እና ጥርጣሬ የችግሩ መሠረታዊ ምንጭ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ይህ ደግሞ ሀገሪቱ በየወቅቱ የምታደርገውን የዴሞክራሲ የሽግግር ሂደት ፈታኝ አድርጎታል።

ይህንን ሀገራዊ ችግር ለዘለቄታው ለመፍታትና ሀገሪቱን ከግጭት አዙሪት ለመታደግ፤ መንግሥት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በአዋጅ አቋቁሞ ወደ ሥራ የሚገባበትን የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሯል። ኮሚሽኑም ከተቋቋመ ማግስት ጀምሮ ከፍ ባለ ኃላፊነት መንፈስ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለሥራው ስኬታማ የሆኑ ሰፊ ሥራዎችን በማከናወን አሁን ላይ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሷል።

ኮሚሽኑ ሆነ የኮሚሽኑ አባላት ምንም አይነት የፖለቲካ ወገንተኝነት በሌላ መልኩ፣ ከማንኛውም የመንግሥት ወይም ሌላ አካል ተጽዕኖ ነጻ ሆነው መንቀሳቀስ የሚችሉበት ሕጋዊ ሰውነት ተላብሰው እንዲቋቋሙ መደረጉ ተልዕኳቸውን ስኬታማ በሆነ መልኩ በታማኝነት እንዲወጡ ትልቅ አቅም ሆኗቸዋል።

የኮሚሽኑ ምሥረታ ሆነ ሀገራዊ እንቅስቃሴው በአገሪቱ መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመሥረት አንድ ትልቅ ርምጃ ተደርጎ እየተወሰደ ነው፤ አካታችና ውጤታማ ሀገራዊ ምክክር በማድረግ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሥርዓት ዘመኑን በሚዋጅ ፅኑ መሠረት ላይ ሊያዋቅር እንደሚችልም ብዙ ተስፋ ተጥሎበታል ፡፡

ይህንን እውነታ ታሳቢ በማድረግም፤ መላው ሕዝባችን የኮሚሽኑ ተልዕኮ ውጤታማ እንዲሆን፣ በተሳትፎ አጋርነቱን እያረጋገጠ ይገኛል። ለዚህም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተሳታፊዎች ምልመላ ዙሪያ የሚታየው የነቃ ተሳትፎ ተጨባጭ ማሳያ እንደሆነ ይታመናል ።

ከዚህ በተጨማሪም የሀገሪቱ የቆዩና አሁነኛ ችግሮች በሰላማዊ ውይይት ዘላቂ መፍትሔ ሊኖረው እንደሚችል የሚታመኑ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር በጋራ ለመሥራት እያሳዩት ያለው ቀና ትብብር፤ ለኮሚሽኑ ተልዕኮ ስኬት ዋነኛ አቅም ስለመሆኑ ብዙም የሚያጠያይቅ አይሆንም ።

በኢትዮጵያ ሊኖር የሚችል ሰላማዊ እና የተረጋጋ የፖለቲካ ምሕዳር ለቀጣናው ሀገራት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብር ትልቅ አቅም ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። ከዚህ የተነሳም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለኮሚሽኑ ተልዕኮ ስኬታማነት ከምሥረታው ጀምሮ እያበረከተ ያለው አስተዋፅዖ ከፍ ያለ እውቅና ሊሰጠው የሚገባና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የኮሚሽኑን መቋቋም ከመደገፍ አንስቶ፣ ከ10 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። የገንዘብ ድጋፉ ኮሚሽኑ ለሥራ ማስፈጸሚያ የሚፈልገው ገንዘብ አንጻር ብዙ ነው የሚባል ባይሆንም፤ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ከገንዘብ ድጋፍ ባሻገር ተመድን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጨምሮ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለኮሚሽኑ የእውቀት፣ የሀሳብ፣ የበጀት እና ሌሎችንም ሁለንተናዊ ድጋፎች እያደረገ ያለበት ሁኔታ፤ እንደ ሀገር ለችግሮቻችን በራሳችን መፍትሔ ለማፈላለግ ለጀመርነው ጥረት ስኬት ትልቅ አቅም ነው፡፡

ይህ ጥረታችን ስኬታማ እንዲሆን ግን ከሁሉም በላይ አሁናዊ ሰላም የሚኖረው አስተዋፅዖ የማይተካ ነው። ከዚህ የተነሳ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሰላም እናቶችና ወጣቶች፣ የሲቪል ማኅበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች/ ሁሉም ዜጎች ከምንጊዜውም በተጠናከረ መልኩ አካባቢያዊና ሀገራዊ ሰላም ለማስፈን ተግተው ሊሠሩ ይገባል ።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እምቅ የቱሪዝም ሀብታችንን ለማልማት ቆርጠን እንነሳ

ሶሎሞን በየነ

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያላት የበርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶች ባለቤት፤ ከ80 በላይ የሚሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች ሀገር ናት። እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦች የየራሳቸው መለያ የሆኑ ባሕላዊ እሴቶች፣ ቅርሶች፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ሥነ-ቃል፣ ወግ፣ ዕምነት፣ እሴትና ሥነ-ጥበብ አሏቸው።

ይህም ሀገሪቱን በሚዳሰሱ (ታንጀብል) እና በማይዳሰሱ (ኢንታንጀብል) ባሕላዊ ቅርሶች ሀብት የበለጸገች አድርጓታል፡፡ በዚህ ረገድ ሀገሪቱ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርሶች መዝገብ ዘጠኝ የሚዳሰሱ (ታንጀብል) እና አራት የማይዳሰሱ (ኢንታንጀብል) ባሕላዊ ቅርሶችን በድምሩ 13 ቅርሶችን በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር ናት።

ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ የቅድመ ሰው ዘር መገኛ ሀገርም ናት። የኢትዮጵያውያን ብሎም የዓለም ሕዝብ ቅድመ አያት የሆነችውን የሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዓመት እድሜ ባለቤት ድንቅነሽ (ሉሲ)፣ የአራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዓመት እድሜ ባለቤት አርዲና የሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዓመት እድሜ ያስቆጠረችው ሰላም የቅድመ ሰው ዘር መገኛ፤ የቅድመ ታሪክ ቅርሶች ባለቤት ናት።

የነዚህ ሁሉ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከፍ ያለ አቅም ሊሆኑ የሚችሉ ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም፤ እነዚህን ሀብቶች በማልማት ተጠቃሚ በመሆን ያላት ተሞክሮ ግን ሲታይ፤ ከዚህ ግባ የማይባል የቱሪዝም ሀብት ካላቸው ሀገራት ያነሰ ስለመሆኑ መረጃች እና የተለያዩ ጥናቶች በስፋት ያሳያሉ።

ለአብነት ከኤስያ ሀገሮች አንዷ የሆነችው ታይላንድ ያላትን ብርቅየ የነብር ዝርያ ላይ ትንሽ ኢንቨስት በማድረግ ለዓለም ሕዝብ በስፋት በማስተዋወቅ፤ የምታገኘው ገቢ ኢትዮጵያ ከጠቅላላው የቱሪዝም ዘርፏ ከምታገኘው ገቢ በእጅጉ ይልቃል።

እንደ ዓለም ቱሪዝም ድርጅት መረጃ የብርቅየ ነብር ዝርያ መገኛ የሆነችው ታይላንድ እ.ኤ.አ በ2019 ብቻ 39 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዓለም አቀፍ ቱሪስት ጎብኝቷታል። በዚህም 60 ሺህ 521 ሚሊዮን ዶላር ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ደረሰኝ (International tourism receipts) ወይም ገቢ አግኝታለች።

ሌላኛዋን የኤስያ ሀገር ቻይና በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ግንባታ ላይ ማኅበረሰቡ በተለያየ መንገድ እንዲሳተፍ በማድረግ የቱሪስት መዳረሻዎቹዋ በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋት እንዲተዋወቁ ማድረግ ችላለች፡፡ በዚህም የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶቿን/ሀብቶቿን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ በዘርፉ ከፍ ያለ ተጠቃሚ ሆናለች፡፡

በአንድ ሰማይ እልፍ ከዋክብት እንደሚደምቁ ሁሉ፤ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር እልፍ የቱሪዝም ሀብት እያሉ በአግባቡ ማየት፣ ማልማት እና ማስተዋወቅ ባለመቻላችን ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ማግኘት ሳትችል ቀርታለች ።

የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ፣ የ900 ዓመት ብራና ቅርስ፣ የራሷ የዘመን አቆጣጠር፣ ...ወዘተ ዘርፈ ብዙ የባሕልና የቱሪዝም ሀብት ባለቤት የሆነችው ሀገራችን፤ የ200 ዓመት ታሪክ እንኳን ከሌላቸው ሀገራት እኩል ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን አልቻለችም።

ለዚህም ደግሞ የአሜሪካንን እና የፈረንሳይን ተጨባጭ እውነታ መቃኘት በቂ ነው፤ እንደ ዓለም ቱሪዝም ድርጅት መረጃ አሜሪካ እ.ኤ.አ በ2022 ብቻ 50 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዓለም አቀፍ ቱሪስት ጎብኝቷታል። ከዚህም 135 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ደረሰኝ (International tourism receipts) ወይም ገቢ አግኝታለች።

በፈረንሳይ የቱሪዝም ዘርፉ እ.ኤ.አ በ2013 ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) 79 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዩሮ በቀጥታ አበርክቷል። ይህ ከኛ ሀገር ጋር

**ሀገሪቱ ባሏት የቱሪዝም ሀብቶች አሁን ላይ በሀገሪቱ ፈተና እየሆነ ያለውን የሥራ አጥነት መቅረፍ የሚያስችል የሥራ ዕድል መፍጠር፣ በዚህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የሥራ ባለቤት ማድረግ እንደሚቻል ይታመናል። ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው ጥረትም ዘርፉ ሊኖረው የሚችለው አበርክቶ ከፍ ያለ ነው**

ሲነጻጸር /በተያዘው በጀት ዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ከተያዘው እቅድ ጋር ሲነጻጸር/ምን ማለት እንደሆነ ለማገናዘብ የሚከብድ አይደለም።

ሀገሪቱ ባሏት የቱሪዝም ሀብቶች አሁን ላይ በሀገሪቱ ፈተና እየሆነ ያለውን የሥራ አጥነት መቅረፍ የሚያስችል የሥራ ዕድል መፍጠር፣ በዚህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የሥራ ባለቤት ማድረግ እንደሚቻል ይታመናል። ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው ጥረትም ዘርፉ ሊኖረው የሚችለው አበርክቶ ከፍ ያለ ነው።

ስለዚህ በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር በመቅረፍ፤ ሀገሪቱ እንደ ሀገር ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ከሁሉም በላይ በዘርፉ ያላትን ሀብት ማወቅ፤ ማልማትና ማስተዋወቅ ይገባል።

ከዚህ አኳያ ከሰሞኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና የሆስፒታሊቲ ዐውደ-ርዕይን በከፈቱበት ወቅት እንደተናገሩት፤ "አሁን ጊዜው ድህነትን የምንታገልበት ብቻ ሳይሆን በተለይ ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት በማውጣት በጋራ የምንለማበት ወቅት ነው።

.... እኛ ከቅንነትና ከትጋት በስተቀር ያጣነው የለም። ስለዚህ ዓይናችን ገልጠን ማየት፣ ያየነውን በማልማት እንዲወጣ ከማድረግ ባለፈ ማስተዋወቅና የአገልግሎት አሰጣጣችን ማሳደግ ከቻልን በጋራ እንለማለን" ብለዋል።

በመሆኑም በተለይ የለውጡ መንግሥት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ከኃያላኑ ተርታ የሚያሰልፍ ጠንካራ ኢኮኖሚ መፍጠር እንደሚቻል አምኖ፤ በዘርፉ እያከናወነ ያለውን ልማት አጠናክሮ ማስቀጠል ይኖርበታል። ነገ ላይም የልማቱ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ የሚሆነው ማኅበረሰቡ በመሆኑ ልማቱን በሚችለው ሁሉ ሊደግፍ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ ከአዳዲሶቹ የመዳረሻ መስሕብ ስፍራዎች ባሻገር፤ ነባር ባሕላዊ፣ ታሪካዊ፣ መልክዓ ምድራዊ ሃብቶችን እንዲሁም ያልተዳሰሱ አዳዲስ የቱሪዝም መስሕቦችንና ዘርፎችን ከተቀበሩበት አውጥቶ በሚገባ አልምቶ፣ አስተዋውቆና ጠብቆ የሀገርንና የዜጎችን ገቢ ማሳደግ ለነገ የማይባል የሁሉም ዜጋ የቅድሚያ ቅድሚያ ሥራ መሆን ይኖርበታል።

# ተጠየቅ

# «የእጅም የልብም ንጽሕና ያለው አመራርና ማኅበረሰብ መፍጠር አለብን ብለን እየሠራን ነው»

- አራርሶ ገረመው (ዶ/ር)፣
የሲዳማ ክልል የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**የሲዳማ ክልል ከተመሠረተ ሦስት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ በርካታ ለውጦችም እየተመዘገቡ መሆኑ ይነገራል፡፡ የክልሉ የፋይናንስ አጠቃቀምና አንዳንድ አሠራሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፉና ከሀገራዊ እቅድ ጋር የተናበቡ መሆናቸውም ይገለፃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች የሚነሱባቸው ጉዳዮችም እንዳሉ ይታወቃል፡፡**

**በዛሬው የተጠየቅ ዓምድ ዕትማችንም የክልሉ የፋይናንስ አሠራርና አጠቃቀም፣ ክልሉን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች፣ መሠረተ ልማቶችን ለማሳለጥና የኅብረተሰቡን ጥያቄ በወቅቱ ለመመለስ እየተከናወኑ ስለሚገኙ ተግባራት እና ከዚሁ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከሲዳማ ክልል የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ አራርሶ ገረመው (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- ከባለፈው በጀት ዓመት በመልካም ተሞክሮ ተወስዶ ወደ 2016 በጀት ዓመት የሚሻገር ምን አሠራር አላችሁ?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** ባለፈው በጀት ዓመት የተመደበው ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ልዩ ትኩረት ሰጥተን ስንሠራ ነበር፡፡ በተለይም በ2015 በጀት ዓመት የክልላችን ፋይናንስ ሥርዓት ዲጂታላይዝ ለማድረግና ከቴክኖሎጂ ጋር ለመሄድ በርካታ ውጥኖችን አስበን ነው ወደ ሥራ የገባነው፡፡ በዚህ ረገድ አጠቃላይ በወረዳ እና በክልል የፋይናንስ ሥርዓት የተዘረጋው የኦን ላይን ሥራ ለመጀመርና ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ነው ታቅዶ የነበረው፡፡

በዚህ ረገድ እንደ ክልል በአጠቃላይ በክልል ማዕከል እና የወረዳዎችን ጨምሮ ካሉን ከ80 በላይ ተቋማት ውስጥ፤ 48 የሚሆኑትን በኦን ላይን ሥርዓት አስገብተናል፡፡ በዚህም የፋይናንስ ሥርዓቱን በአንድ ተቋማት የመመልከትና የማየት ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፤ ይህን 38 ከመቶ አሳክተናል፡፡ ቀሪውን በ2016 በጀት ዓመት ለማሳካት እቅድ ይዘናል፡፡

ሌላው በ2015 ለውጥ ለማምጣት ስንተጋ የነበረው፣ ቀደም ብሎ የነበረው ዝርክርክ አሠራር ማዘመንና ባለሙያዎችን ማሠልጠን ነበር፡፡ ይህን መቶ በመቶ አሳክተናል፡፡ ሌላኛው እንደ ሀገርም ለመንግሥት ትልቅ አቅም የሚሆነውና አብዛኛው ሃብት የሚውለው ግዥ ላይ ነው፡፡ 60 ከመቶ ሃብት የሚውለው እዚህ ላይ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በፌደራል የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት መሠረት 70 ተቋማት ጥቅም ላይ አውለዋል፡፡ እንደ ክልላችንም በፌደራል የተጀመረ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት በመጀመር የመጀመሪያው ነን፡፡ በ2015 የግንዛቤ ማስጨበጫ ላይ አትኩረን ሠርተናል፡፡ በ2016 ሙሉ ትግበራውን እንጀምራለን፡፡

በአጠቃላይ በ2016 በጀት ዓመት ሐዋሳ ከተማ ጨምሮ 12 ቢሮዎች ይህን ሙሉ ትግበራ እንዲጀምሩ ሥልጠና ሰጥተን አጠናቀናል፡፡ አሁን ድህነት ቀናሽ የሚባሉ ሰባት ተቋማትና ከፍተኛ ሃብት የሚንቀሳቀስባቸው ከፍተኛ በጀት ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ወደዚህ ሂደት በቅርቡ ይገባሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኤሌክትሮኒክስ ግዥ እና የኦንላይን ሥርዓት ትግበራ በመጀመራችሁ እንደ ክልል ምን አተረፋችሁ?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** ሩቅ ለሚገኝ ወረዳ ወይም ሴክተር ቢሮ ዋናው የፋይናንስ ተቋማት መረጃ ያለው በፋይናንስ ቢሮ ነው፡፡ ቀደም ሲል ስንጠቀም የነበረው ሥርዓት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ገብቶ የሚስተካከል ወይንም በባለሙያ የሚታረም ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ሪፖርቶች ላይ መጨመርና መቀነስ ይቻል ነበር፡፡ ይህም ለአሠራር አስቸጋሪ ነበር ፡፡

አሁን ያለው ግን ይህን ያስቀረ ነው፡፡ ይህም ከአንድ ማዕከል በመሆን በሌሎች ሴክተሮች በፋይናንሱ ላይ ምን እየተከናወነ ነው የሚለውን ማወቅና መቆጣጠር ተችሏል፡፡ ጠቅለል ሲደረግ ቀደም ሲል የነበረው የሪፖርት አቀራረብ፣ የሃብት አጠቃቀም ላይ ችግሮች ነበሩብን፡፡ ስለዚህ ይህን ማስቀረት ተችሏል፡፡ የሁሉንም ቢሮ የፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘምን አስችሏል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህ አሠራር በፕሮጀክቶች ላይ ያለውን ሙስናን ለመከላከል አስችሏል ማለት ነው?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** አዎ! ቀደም ሲል አንድ ሰው ሥራውን ሳይሠራ አድቫንስ ይወስዳል፡፡ አሁን ግን በሲስተም የሚመራ ስለሆነ ያልተሠራበት አይከፈልም፡፡ በመሆኑም ሙስና ለማስቀረት ትልቅ አቅም አለው፡፡ በኦንላይን ሥርዓትም የሚመዘገብ ሥርዓት ስለሆነ ማጭበርበር ወይንም ለሙስና የመጋለጥ ዕድሉ በጣም ጠባብ ነው፡፡ ስለዚህ በጣም ጥቅም አለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ጥቅም እንዳለው ሁሉ «ፍሌክሲብል» ለመሆን ፈተና አይሆንም?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** ቴክኖሎጂ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ጉዳት ሊኖረው ይችላል፡፡ ከላይ በገለጽኩት መንገድ ጉዳት የለውም፡፡ ችግር የለውም ማለት ግን መቶ በመቶ ነው ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን አሁን ለምንሠራው ሥራ ጠቅሞናል፡፡ ለምሳሌ ይርጋለም ላይ ለሚሠራ ሥራ የሂሳብ ማጭበርበር እንዳይኖር ከማዕከል ሆኖ መቆጣጠር ይቻላል፡፡ ይህ ፋይናንስ ሥርዓት የዘመነ ለማድረግና አጠቃቀሙም በዚሁ ደረጃ በሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ነው የተደረገው። ስለዚህ በሲስተም የሚመራ በመሆኑ ብዙ ችግሮችን የሚያስቀር መሆኑን ግንዛቤ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ የፋይናንስ ሥርዓት ማዘመኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ አጠቃቀሙና ልማቱ በዋና ከተማ ሐዋሳ ላይ በማተኮሩ ሌሎች ከተሞችና ወረዳዎችን ዘንግቷል የሚል ወቀሳ አለ፡፡ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** ይህ መረጃ በአግባቡ መታየትና መታረም አለበት፡፡ እንዲያውም የምንታማው ሐዋሳን ዘነጋችሁ በሚል ነው፡፡ ባለፉት ሦስት ዓመታት በሲዳማ ክልል የተሠራው ላለፉት 40 ዓመታት ያልተሠራ የመንገድ ሽፋን ተደራሽ ማድረግ ችለናል፡፡ 1ሺ600 ኪሎ ሜትር በላይ ጠጠር መንገድ ገንብተናል፡፡ በዚሁ ሦስት ዓመት ውስጥ 2ነጥብ3 ቢሊዮን ብር በላይ ለገጠር መንገድ ግንባታ ወጪ አድርገናል፡፡ ለከተማ ልማትም 1ነጥብ1 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ አድርገናል፡፡ ይህ ከተለያዩ አካላት የሚመጣው ሳጨመር መንግሥት የመደበው ሃብት ነው፡፡

በውሃ ልማትም በሰፊ የተሠራ ሲሆን ሲዳማ በ2012 ዓ.ም ዞን በነበረበት ወቅት የነበረው የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን 38 በመቶ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የግብረ ሠናይ ድርጅቶችን ትተን ሽፋኑ 56ነጥብ3 በመቶ ደርሷል፡፡ ለዚህም 1ነጥብ1 ቢሊዮን ብር ወጪ አድርገናል፡፡ ስለዚህ የምናከውናቸው የልማት ሥራዎች ፍትሐዊነትን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም በሲዳማ ክልል የነበረውን የፍትሐዊነት መጓደል ጉዳይ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ከገጠር እስከ ከተማ በመሠረተ ልማት በማስተሳሰር ረገድ በጥሩ አካሄድ ላይ ነው፡፡


ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

ቀደም ሲል የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር በነበረንበት ወቅት እስከ 10 ዓመት ተጓተው የነበሩ ከ40 በላይ ድልድዮችን ያጠናቀቅነው በሦስት ዓመታት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ አሁናዊ እይታችን አጠቃላይ ሲዳማን ማሳደግ ነው። ሐዋሳ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ነው፡፡ ከመንግሥት ትሬዠሪ አይሰጠውም፡፡ ስለዚህ ትልቁ ትኩረት ለገጠሩ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

የእኛ እይታ ሁሉም ወረዳዎች በራሳቸው ገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ ነው፡፡ በዚህ ዓመት ሐዋሳ እና ወንዶ ገነት የራሳቸውን ወጪ መቶ በመቶ እንዲችሉ ነው የተደረገው፡፡ አለታ ጩኮ 80 ከመቶ ሸፍኗል፡፡ ወረዳውም 70 ከመቶ በላይ እንዲደርስ አድርገናል። ይሁንና ከፍትሐዊነት አኳያ መንግሥት በጀት ይዞ በእነዚህ ከተሞችም የሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች አሉ፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ወቅት የፕላን ቢሮ ከሥርጭት አኳያ እያጠናው ያለው ጥናት አለ፡፡ ምን ያክል ሽፋን፣ ርቀት፣ እንዴት ተከናወነ የሚሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ አንዳንዱ አካባቢ መልክዓ ምድሩ ላይ አራት ኪሎ ሜትር መንገድ በሚሠራበት ሃብት ሌላ መልክዓ ምድር ላይ 25 ኪሎ ሜትር ሊሠራ ይችላል፡፡ ይሁንና ይህን በአግባቡ ለመመለስ የሚያስችለው ጥናት በመሆኑ ወደዚህ ተገብቷል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ሦስት ዓመታት በሁሉም መስክ 514 ፕሮጀክቶችን ማከናወን ችለናል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች የት አካባቢ እንደተሠሩ በደንብ ይታወቃሉ፡፡ ይህ ብዙ ፕሮጀክት ነው፡፡ በየዓመቱ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ነው የምንመድበው ። ባለፉት ሦስት ዓመታት ሐዋሳ ከተማን ጨምሮ 13 ቢሊዮን ብር ከመንግሥት ካዝና ወጪ አድርገናል። ይህ ቻናል አንድ፣ ሁለት እና ሦስት የሚባለውን አያጠቃልልም፡፡ ስለዚህ እንደ ክልል ድህነትን በሚቀንሱ ፕሮጀክቶች ላይ አተኩረናል፡፡ ይህ እንደ ሀገርም ተመሳሳይ ነው፡፡ በክልላችን ለድህነት ቅነሳ የሚያግዙ እንደ ግብርና፣ ትምህርት፣ ጤና፣ እና መሰል ሴክተሮች ላይ እስከ 61 በመቶ በጀት እየመደብን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሲዳማ ክልል ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግትና የመሬት ጥበት ያለበት ነው። ይህን ከገቢ አሰባሰብ፣ ፋይናንስ አጠቃቀምና የዘመነ አሠራር ከማስኬድ አኳያ ምን እየተሠራ ነው?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** ገቢ አሰባሰቡን ማዘመን ከፍተኛ ትግል የሚጠይቅ ነው፡፡ ዲጂታላይዝ ከማድረግም አልፎ ትውልድ ላይ ስለ ግብር አስፈላጊነት በደንብ መሠራት አለበት፡፡ በዚህ ላይ ገቢዎች ቢሮ የራሱን ሥራ እየሠራ ነው፡፡ እውቅና ከመስጠት ጀምሮ ብዙ እየተሠራበት ነው፡፡ ከታችኛው መዋቅር ጀምሮ እየተንቀሳቀስን ነው፡፡

እንደ ሲዳማ ክልል የተጠጋጋ ማኅበረሰብ ያለበትና የመሬቱም ስፋት መጠነኛ ነው፡፡ ከጥቂት አርብቶ አደሮች በስተቀር በሄክታር የሚቆጠር መሬት የላቸውም፡፡ ሌላው እንደ ሲዳማ የሚያሳስበው ከተሜነት እየተስፋፋ ነው፡፡ በየሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ከተማ ይገኛል፡፡ ከ72 በላይ ከተሞች በማዘጋጃ የተያዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማዘጋጃ ገቢውም በዚያው ልክ መጨመር አለበት፡፡ ስለዚህ እነዚህን እቅዶች በስትራቴጂ በ10 ዓመቱ እቅድ እና በአምስት ዓመቱ እና በሦስት ዓመቱ የሚከናወኑት ምንድን ናቸው ለሚለው ፍኖተ ካርታ አለን፡፡

ሲዳማን እንዴት እንመራለን በሚለው ላይ ቀጣይነት ያለው ዕድገት ላይ በተለይም ደግሞ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ጋር በትይዩ የሚሄድ ነው፡፡ አካሄዳችን ቀጣይነት ያለው ዕድገትን መሠረት አድርገን ነው፡፡ በተለይም በፋይናንስ እና

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## «የእጅም የልብም ንጽሕና ያለው አመራርና...

ከገጽ 6 የዞረ

ኢኮኖሚክስ ሴክተሩ የመጀመሪያ ትኩረታችን ሰው ተኮር መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ ሰው መማር፣ መብላት፣ መጠጣት አለበት፡፡ ስለዚህ ሥራችን ሰው ተኮር መሆን አለበት፡፡

ይህን ለማድረግ ደግሞ ገቢ ያስፈልጋል፡፡ ሊሠራ የሚችለው በገቢ ነው፡፡ የብሔራዊ ባንክም ቢሆን እንደ ክልል ብሎም እንደ ሀገር የተሰባሰበውን ገቢ ድምር ውጤት ነው የሚመድበው፡፡ በመሆኑም የተሰበሰበው ተመልሶ እንደሚሰራጭ ይታወቃል። ስለዚህ ይህን ለማድረግ ሲዳማ ክልል 2012 ዓ.ም ወይም ደግሞ ሲዳማ ክልል ከመሆኑ በፊት ወጭ የመሸፈን አቅሙ 20 በመቶ ነው፡፡ ስለዚህ ግንዛቤን በማሳደግ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሠራተኛው በቁርጠኝነት በሠራው ልክ የሚመዘን ነው፡፡ በ2015 በጀት ዓመት 44 ከመቶ በላይ በውስጥ ገቢ መሸፈን የቻለ ክልል ሆኗል፡፡ ስለዚህ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በእጥፍ አድጓል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ሥራ እየተሠራ ያለው በዚህ ልክ ነው፡፡ በዚህ ዓመት ከ55 በመቶ የክልሉን ወጭ በውስጥ ገቢ የመሸፈን ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡ ይህ ለሀገር እንደ ትልቅ ትምህርት የሚወሰድ ነው፡፡

የክልሉ ገቢ ትልቅ አቅም እየሆነ ነው፡፡ ገቢ ሲኖር በክልሉ ልማት እንዲፋጠን የማድረግ አቅም ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ወንዶገነት ላይ የሚጨነቁት ምን ልሥራ እንጂ እንዴት እንሥራ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በቀን ምን ያህል ገቢ እንደሚሰበሰብ ሲታይ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩ አሠራሮችን የማዘመን ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ በአጠቃላይ አሠራራችንና ዕይታችን ሰው ተኮር ነው፡፡ ሥራው ምን ያህል ውጤት አመጣ፤ እንዴትና በምን መልኩ የሚለው በአሠራሩ መሠረት እየታየና እየተገመገመ የሚሻሻልና የሚጠናከር ነው፡፡

ሦስተኛው ሰላምን ማስጠበቅ ነው፡፡ ማንም ሰው በሰላም ወጥቶ በሰላም ሲገባ ነው መግባት አለበት፡፡ ኢኮኖሚውም የሚፈልገው ሰላም ነው፡፡ ሰላም ከሌለ መብላት፣ መጠጣት አያምርም፡፡ ስለዚህ ሥራችን ሕዝብ ተኮር ነው፡፡ ኢኮ-ሲስተሙ ዕቅድ ተኮር ነው፡፡ አረንረጓዴ አሻራም ይሁን ሌሎች ተግባሮች በመናበብ የሚሠሩ ሲሆን ሰላምን የማስፈን ጉዳይ እንደ ትልቅ መፈክር ሆኖ የሚሠራበት ነው፡፡ ሁሉም ሰው በልኩ መሥራት የሚችልበት፤ አካባቢው ከራሱ አልፎ ለሌሎች ምቹ የሚሆንበትን ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

ለዚህም የወንድማማችነት ስሜት በክልሉ እንዲፈጠር ይሠራል፡፡ ደጋፊ አካላትና ረጂ ድርጅቶች ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ ነው፡፡ ብልጽግናን በዘርፈ ብዙ እይታ እንመለከተዋለን፡፡ መሠረተ ልማት ማሟላት አንዱ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ በሞተርም ይሁን በሌሎች ተሽከርካሪዎች በሰላም ወደ ቤቱ ገብቶ ምቾት ካልተሰማው ብልጽግና አይረጋገጥም። የመንገድ መሠረተ ልማት፣ የግብርና ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ማሟላት ላይ በስፋት እየተሠራ ነው፡፡ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት፤ ሥልጠናዎችን መስጠት፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምርትና ምርታማነት መቀነስ ማለት ቀጥተኛ ያልሆነ የዋጋ ግሽበትን መፍጠር ነው፡፡ እይታው ሁሉን አቀፍ ነው፡፡ ከ40 ዓመት በኋላ ክልሉ የት ይደርሳል የሚለውን ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢንቨስተሮች በክልሉ እንዲሠማሩ አሠራሩ የዘመነ አትራፊነት እንዲጨምር ከማድረግ አንጻር እንደ ፋይናንስ ቢሮ ምን ተሠርቷል?**

**አራርሳ (ዶ/ር)፡-** ይህን በሁለት መልኩ ማየት ተገቢነት አለው፡፡ 80 በመቶ በላይ ክልሉ የሚዋሰነው ከኦሮሚያ ክልል የሚወሰን ሲሆን ቀሪው በቀድሞ አጠራር ከደቡብ ክልል የሚዋሰን ነው፡፡ ልማት ድንበር፣ ወገን፣ ጎሳ የለውም፡፡

ቡራ ጋጣ የምትባል ከተማቸው ናት፡፡ ከእኛ ከድንበር 10 ኪሎ ሜትር ጠጠር መንገድ አሠራን። ቡራ ላይ የኦሮሚያ አመራር ባለቡት መንገዱ ይመረቃል፡፡ ሕዝብን እንደ ሕዝብ ለማገናኘት ኢኮኖሚ ወሳኝነት አለው፡፡ መንገድ የሆነ ክልል ላይ ይጀምርና ጫፍ ላይ ሄዶ ይቆማል፡፡ ይህ ትክክል አይደለም፡፡ መንገድ እንደ ሀገርም የሚፈጥረው ምስል የሚያመጣውም ጠቀሜታ ቀላል አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ኮሪደሩ በጣም አስቻጋሪ ስለሆነ ብዙ ጥንቃቄ እንደሚፈልግ እናስባለን፡፡

ሲዳማ ውስጥ መጥቶ ማንኛውም ባለሃብት በፈለገው ሁኔታ ባሰበው ከተማ ላይ ሂዶ ማልማት ይችላል፡፡ ስለሆነም በክልሉ ኦሮሚያ እና የመሰሉ በርካታ የሌሎች አካባቢ ባንኮች አሉ፡፡ በዚህ ዓመት የእኛንም ቢሮ ጨምሮ በአጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱ ክፍያውን ቼክ ፍሪ ልናደርግ አስበናል። ቼክ ጋር ተያይዞ እንደሀገርም የተጀመረ አቅጣጫ አለ፡፡ እንደ ክልል አሁን ከንግድ ባንክ ጋር ውል ገብተን በቢሮ ልንጀምር አስበናል፡፡ ወደ ቴክኖሎጂ መግባቱ አጠቃላይ ሥርዓቱን ለማዘመንም ዕድል ስለሚሰጥ በልዩ ትኩረት እየሰራን ነው፡፡ በአጠቃላይ ከአጎራባች ክልሎች ጋር ያለንን ሠላም የተረጋጋ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሲዳማ ክልል በኬንያ እና በአጎራባች ሃገራት ኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎች እንደሚካሄድበት ይታወቃል፡፡ በዚህ ላይ እንደ ክልል ምን እየተሠራ ነው?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** የኮንትሮባንድ ጉዳይ ሃገራዊም ችግር ነው፡፡ እንደ ሀገርም የምንፈተንበት ነው፡፡ ሰው ወደ ሕሊናው፣ወደ ቀልቡ እስኪመለስ እና ኢትዮጵያን ወደ መውደዱ ተመልሶ አርበኛ እስኪሆን ድረስ ሰፊ ሥራ እንሠራለን፡፡ ይህች ሃገር ማግኘት ያለባትን ጥቅም፤ መድረስ ያለባትን ጎዳና፤ መድረስ ወዳለባት ከፍታ የምንጓጓው የምንመኘው ብልጽግና እንድትደርስ ዝርክርክ እንደ እኛ ለማይመጥኑ ሥራዎች ዕድል አንከፍትም፤ በርም አንሰጥም፡፡ በዚህ ላይም ከፍተኛ የሆነ የቁጥጥር ሥርዓት እና የጥንቃቄ ሥራዎችን እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ከማዳበሪያ ዕዳ አመሳሰስ ጋር በተያያዘም ወቀሳዎች ይሰነዘሩበታል፡፡ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ የዕዳ ቀንበር ያለበት ነው፡፡ እሱም የማዳበሪያ ዕዳ ነው፡፡ የነበረው አሠራር፤ የነበረው ሥርዓት እጅግ ጥሩ የማይባል ነበር፡፡ እኛ ክልል ሆነን የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊነት 2013 ዓ.ም ላይ ስንመጣ ከገንዘብ ሚኒስቴር ወደ 588 ሚሊዮን ብር ዕዳ ነው የወሰድነው፡፡ እንደሚታወቀው፤ የማዳበሪያ ዕዳ ወለድ አለው። ወለዱ ደግሞ ኮምፓውንድ ሬት ነው፡፡ በየዓመቱ ይጨምራል፡፡ ከ2007 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ 747 ሚሊዮን ብር ዕዳ ከፍለናል። በአጭሩ በወቅቱ የነበረውን ጨርሰናል፡፡ ይሁን እንጂ በ2012 ዓ.ም አልከፈላችሁም፤ የሚል ቅሬታ እየመጣ ነው፡፡

የጠፋው ሃብት የት ነው ተብሎ ቢጠየቅ ሚስጥሩ በጣም ከባድ ነው፡፡ በወቅቱ የነበረው የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የሚባል ተቋም አለ፡፡ ኤጀንት የሚባል አለ፡፡ እኛ ከሕዝቡ ዕዳ አውርደናል፡፡ ቀጥሎ ይህን የወሰደው ማን ነው? የሚለውን በኦዲት ፈልገን ወደ ዘመቻ ልንገባ ነው፡፡ ኦዲት ያላደረከውን ግን እከሌ ነው ማለት አይመችም፡፡

ግን ኦሞ ይሰጥ ነበር፡፡ ኦሞ ውስጥ ኤጀንት ነበር። ኮፕሬቲቭ ውስጥ አመራር አሉ፡፡ በዚህ በርካታ ተዋንያን አሉ፡፡ ያንን ሕያው ለማድረግ በአሁኑ ወቅት እየሠራነው ባለው ኦዲት ነው፡፡ ከዛም የሕግ ተጠያቂነት አለ፡፡ ይህ ዕዳ ተመልሶ ሃብት መሆን አለበት፡፡ ብር ሆኖ ወደ ልማት መግባት አለበት የሚል አቋም አለን፡፡ ሌላው በ2013 ዓ.ም መንግሥት ስንሆን ያደረግነው ወሳኝ ነጥብ ከኦሞ እጅ ነጥቅን፡፡ ይህን አወዳድረን ለአንድ ዩኒዮን ሰጠን፡፡ አሁን ካሽ ነው የምንሸጠው፡፡ እጅ በእጅ ሲሆን ደግሞ እንደ ዱሮ አይደለም፡፡ በዚህ መንገድ 94 ከመቶ ሥራችንን ማሳካት ችለናል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ይህ ጉዳይ አሁንም ቢሆን የማዳበሪያ ገበያ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ የሥራ ኃላፊዎች ተጠያቂ ሆነዋል፡፡ በዚህ ዓመት በራሱ ማዳበሪያ ላይ በማጭበርበራቸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው አመራርና ባለሙያ ተጠያቂ ሆነዋል፡፡ በእዳውም የሚጠየቁ አካላት አሉ፡፡ አስጠይቆ የማስከፈል ሥራ ደግሞ የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡ እኛ በዚህ ላይ ያለን ቆራጥነትና ላቅ ያለ ነው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ሰዎችን እየመከርን፣ እያስተማርን፣ እየገሰፅንና እያሠለጠንን እያስተካከልን እንሄዳለን፡፡ በአጠቃላይ ግን በርካታ ሰዎች በማዳበሪያ ጉዳይ ተጠያቂ ሆነው በአሁኑ ወቅም በሕግ ከለላ ሥር ያሉ አሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በተያዘው በጀት ዓመት ከሚያገኘው ገቢ ስታስመስት ዓላማ የማዋልና የፋይናንስ ግልጸኝነት ከማስፈን አኳያ ምን እየሠራ ነው?**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** በዚህ ዓመት አጠቃላይ በጀታችን 22ነጥብ6 ቢሊዮን ብር ነው፡፡ ይህ ከትሬዠሪ እና አንዳንድ አሲስታንት ጋር ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 13 ቢሊዮን ብር ከውስጥ ገቢ ነው፡፡ ይህ ሃብት በጣም በትልቅ ቅልጥፍና፣ የፖለቲካ አመራርና ቁርጠኝነት ሰብስቦ ልማት ላይ ማዋል ይገባል። ይህ እንዲሳካ ሌት ተቀን እንሠራለን፡፡ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሕዝብ ፍላጎት ማርካት አለብን፡፡

ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማት ፍላጎት አለው፡፡ ይህን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት እየሠራን ነው፡፡ የክልሉ የገቢ ምጣኔም በየጊዜው እያደገ ነው፡፡ 2013 ዓ.ም አጠቃላይ ገቢው አንድ ቢሊዮን ብር አይሞላም ነበር፡፡ በዚህ ሦስት ዓመት ውስጥ ግን እጅግ በብዙ እጥፍ አድጓል፡፡ ዕድገት እንዲመጣ ግን የእጅም የልብም ንጽሕና ያለው አመራርና ማኅበረሰብ መፍጠር አለብን ብለን ጥረት እያደረግንም፤ እየሠራንም ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ሳደረጉት ቆይታ እናመሰግናለን፡፡**

**አራርሶ (ዶ/ር)፡-** እኔም በክልሉ አጠቃላይ የፋይናንስ አሠራር እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ እንድሰጥ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡



> ሰላም ከሌለ መብላት፣ መጠጣት አያምርም፡፡ ስለዚህ ሥራችን ሕዝብ ተኮር ነው፡፡ ኢኮ-ሲስተሙ ዕቅድ ተኮር ነው፡፡ አረንረጓዴ አሻራም ይሁን ሌሎች ተግባሮች በመናበብ የሚሠሩ ሲሆን ሰላምን የማስፈን ጉዳይ እንደ ትልቅ መፈክር ሆኖ የሚሠራበት ነው፡፡

# ለተሻሻለው የትምህርት ፖሊሲ ተግባራዊነት እንሥራ

**ሰው መሆን**

በፍጥነት ተቀያያሪ በሆነው ሉላዊ ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የማያቋርጥ የእድገት ሰንሰለት መኖሩ የግድ ነው። ለዚህ ደግሞ በቴክኖሎጂ፣ በምርምር እና በፈጠራ ውጤቶች መደገፍ አስፈላጊ ነው። ለእነዚህ እውን መሆን ደግሞ ትምህርት አይተኬ ሚና ይኖረዋል። ትምህርት የሰው ልጅ ለእድገትና ለለውጥ በሚያደርገው ትግል ውስጥ ትልቁ አቅም/መሣሪያ ተደርጎ ይቆጠራል። አዳዲስ ግኝቶቹን እና በዓመታት ውስጥ የተከማቹ እሴቶቹን የሚያስተላልፍበት ሂደትም ነው።

በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ትምህርት ግለሰቦች እና ማኅበረሰቡ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። ለሕልውና፣ ለልማት፣ ለእውቀት፣ ችሎታን ለማዳበር፣ ችግር ለመፍታት፣ የማድረግ አቅምን ለማሳደግ እንዲሁም የተዛቡ አመለካከቶችን በማሻሻል የማያቋርጥ የእድገት ሂደት ለማምጣት ወሳኝ ነው።

ከላይ ለማንሳት የሞከርኩት ርዕሰ ነገር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያንም የሚሠራ ነው። ለዚህም ነው ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በራሳችን ባሕል፣ እሴት፣ እውቀትንና ክህሎትን የማስተላለፊያ መንገድ ትውልዱን በትምህርት ስናንፅ የነበረው። በጥንታዊው ኢትዮጵያ የታሪክ መዛግብትም እውቀት፣ ጥበብ፣ የፈጠራና ምርምር አቅም የሚያሳዩ ማስረጃዎች አሁንም ድረስ ሕያው ሆነው ያሉት ።

ከጥንታዊው የትምህርት ሥርዓት ወጣ ስንል በዘመናዊው ዓለም፤ ከለውጥ ሂደቱ ጋር የሚያስተሳስራት ስትራቴጂ በመዘርጋት ውጤት ለማምጣት ሙከራ ስታደርግ ቆይታለች። እነዚህ ሙከራዎች በሥርዓት ለውጥ፣ በርዕዮተ ዓለም ፍልስፍና ቶሎ ቶሎ መቀያየር የተነሳ ከጥራት ጋር የሚያያዙ ጉድለቶች እንዲታዩ አበርክቶው ከፍያለ ሆኗል ።

ከመንግሥት ለውጥ ጋር አብረው የሚለወጡ የትምህርት ፖሊሲና ፍልስፍናዎች በፈጠሯቸው ጫናዎች ወጥ የሆነ፣ በክህሎት፣ በእውቀት፣ በፈጠራ፣ በምርምር፣ በቴክኖሎጂ፣ በተግባር ትምህርቶች የላቀ ትውልድ ማፍራት ላይ የሚያተኩር ሥርዓት እስካሁን ለመዘርጋት አዳጋች ሆኖ ቆይቷል።

በወረቀት ላይ ምሉዕ የሚመስሉ ድንጋጌዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች በፖሊሲውና እርሱን የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ቢቀመጡም በተቀናጀና ስልታዊ በሆነ አግባብ ተግባራዊ ሲደረጉ ሳይቻል አስርተ ዓመታቶች አልፈዋል። የዚህ ውጤትም በትምህርት ሥርዓት ውስጥ አልፈው የሚመረቁ ባለሙያዎች ከፅንሰ ሀሳብ በዘለለ ችግሮችን የሚፈቱ፣ ተግባር ላይ የጠነከሩ፣ የፈጠራና የአዳዲስ የምርምር ውጤቶችን የሚያፈልቁ እንዳይሆኑ ምክንያት ሆኗል። ይህም በጥቅል ሀገራዊ ልማትና እድገት ላይ እንቅፋት ፈጥሯል።

ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በተወሰደው ጠንካራ ክትትልና የተቀናጀ የፈተና አሰጣጥ ማሻሻያ ምክንያት የተገኘው ውጤትም ይህንኑ የሚያሳይ ነው። የተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል፣ በትምህርት ገበታቸው ላይ ዝቅተኛ አፈፃፀም ማሳየትና መመዘኛ መስፈርቱን አለማሟላት ከላይ ያነሳናቸው ቁልፍ ችግሮች የፈጠሩት እንደሆነ ፍንትው አድርጎ አሳይቶናል። በጥራት ያልተማረ ምሩቅ መምህር ይሆናል፤ መምህሩ ደግሞ ተመሳሳይ ተማሪዎችን አስተምሮ ያስመርቃል (ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ)።

ለዓመታት በኢትዮጵያ ብቁና ሀገርን ተረከበው ወደ እድገትና የሚወስዱ ወጣቶች እንዳይፈጠሩ የተከተልነው የትምህርት ሥርዓት ጋሬጣ ሆኖ ቆይቷል። የመፍጠር አቅማቸው ጠንካራ፣ ፅንሰ ሀሳብን መሬት ላይ አውርዶ የማኅበረሰቡን ቁልፍ ችግሮች የሚፈታ እንዳይሆን የምንከተለው የመማር ማስተማር ዘዴ ወንዝ የማያሻግር እንደነበር የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ያምናል። ከዚህ መነሻ “ለመሆኑ የትምህርት ፖሊሲ፣ የመማር ማስተማር ዘዴያችን ምን ይዘት ነበረው? አሁንስ በምን መልኩ መሻሻል ይገባዋል?” የሚሉትን ጉዳዮች እንደሚከተለው ለመመልከት እንሞክር።

> **ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግሥት የትምህርት ሥርዓቱን ለማሻሻልና ጥራትን ለማስጠበቅ ቁርጠኝነትን እያሳየ ነው። ለዚህም ፖሊሲን ጨምሮ ልዩ ልዩ የአሠራር ሥርዓቶችን እያሻሻለ ይገኛል። በቀዳሚነት ግን ባሳለፍነው ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ «የትምህርት አሰጣጣችንና ትውልዱ» ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሽፍንፍኑን ገላልጠን ማየት ችለናል**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የካቲት 20 ቀን 2015 ዓም አንድ ውይይት አድርጎ ነበር። የዚህ ምክክር ማጠንጠኛ የነበረው በ1986 ዓም ተረቅቆና ፀድቆ ወደ ሥራ የገባው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ማሻሻያ ላይ ነበር። በዚህ ውይይት ላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን ማሻሻል ያስፈለገበት ዋንኛ ምክንያት ተገልፆ ነበር። በተሻሻለው በዚህ ፖሊሲ ላይም በክፍል ሁለት “መነሻ ምክንያቱን” በመግለፅ እንዲህ የሚል ሀሳብ ሰፍሮ እናገኛለን።

“....የትምህርት ጥራትም እያሽቆለቆለ የመጣ ሲሆን እንደ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው በየደረጃው ያሉ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የትምህርት ውጤት በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን 50 በመቶና በላይ ውጤት ማምጣት አልቻሉም። ሥርዓተ-ትምህርቱም በንድፈ ሃሳብ የታጨቀ ለነባራዊ የሀገሪቱ ሁኔታዎች ምላሽ የማይሰጥ የሀገር በቀል እውቀትን ያላካተተ፣ በየጊዜው የማይፈተሽ፣ ዜጐችን በግብረገብና በመልካም ሥነ ምግባር በበቂ ሁኔታ ያላነፀ ከመሆኑም በላይ ለሥራ ፈጣሪነትና ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያዘጋጅ አልነበረም።

”መምህራንም ብቃትን ተላብሰው ተማሪዎችን በመረዳትና በመርዳት እንዲሁም ከሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ በማድረስ ረገድ ውስንነት ያለባቸው ሲሆን ትምህርት ቤቶችም ቢሆኑ ለመማር ምቹ ያልሆኑ አስፈላጊው ግብዓት ያልተሟላላቸውና ትምህርቱንም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አስደግፈው የሚሰጡ አይደሉም....” ይላል።

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን ለማሻሻል እንደ መነሻ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ከላይ ያነሳነው አመክንዮ ዋንኛው ነው። መንግሥት ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ውስጥ የትምህርት ሥርዓቱን ለማሻሻል በርካታ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ ትውልዱ በተሻለ የትምህርት ጥራት ተምሮ እንዲያልፍና የሀገርን የልማት አጀንዳዎች እንዲያስፈፅም፤ ኢትዮጵያንም ወደከፍታው እንድትወጣ አጋዥ ኃይል እንዲሆን እየሠራ መሆኑ ነው። በዋናነት ግን የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ቁልፍ ችግሮች ውስጥ የዛሬው ማጠንጠኛችን የሆነው የተሻለና ጥራት ያለው ትምህርት ማቅረብ ያልተቻለበት ምክንያት ነው።

ከላይ እንደተመለከተው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን እንዲሻሻል ገፊ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ “የትምህርት ጥራትም እያሽቆለቆለ” መምጣት ነው። ለዚህ ደግሞ ተማሪዎች ከተግባር ይልቅ ንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ ያተኮረ ትምህርት እንዲወስዱ መደረጉን ይሄው ማስረጃ ይነግረናል። እዚህ ላይ ተመርኩዘን ያለፉትን አንድና ሁለት ዓመት የተመዘገቡ የሀገር አቀፍ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎችን ውጤት እንመልከት።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በተዘረጋው ጥብቅ ቁጥጥር እና የፈተና አሰጣጥ ሥርዓት ምክንያት ብዙኃኑ ተማሪዎች ከ50 በመቶ በታች ያመጡ ሆነዋል። ከሰሞኑ ብቻ የትምህርት ሚኒስቴር ያስፈተናቸው ከ800 ሺህ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ውስጥ 3 በመቶ የሚሆኑት ብቻ ጥብቅ ክትትልና የተከተለውን የፈተና አሰጣጥ ሥርዓት ማለፍ ችለዋል። ከእነዚህ ውጪ ያሉት ብዙኃኑ ተማሪዎች ከ50 በመቶ በታች ያመጡ አብዛኞቹ ደግሞ እጅግ ዝቅተኛ የሆነ ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው።

ከዚህ መረዳት የምንችለው ላለፉት በርካታ አስርተ ዓመታት ስንከተለው የነበረው የትምህርት ሥርዓት ከስር መሠረቱ ችግር እንደነበረበት፤ ስር ነቀል ለውጥ ሊደረግበት እንደሚገባ ነው። ትውልዱ በትምህርቱ የተሻለ ውጤት እንዳያመጣ ከእራሱ፣ ከቤተሰብ፣ ከትምህርት ቤትና መምህር ጀምሮ በየደረጃው ያሉ አካላት ኃላፊነት ቢኖርባቸውም በዋናነት ግን የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ባላገናዘበ ሁኔታ የተቀረፀው “የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ” እንዲሁም አስፈፃሚ አካል የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ እንዳለበት መገንዘብ አያዳግትም።

ለትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው መሻሻል ገፊ ምክንያት ካልናቸው መካከል “በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ከኢንዱስትሪው ጋር የተሳሰረና የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ትምህርትና ሥልጠና አለመሰጠቱ፤ በቂና ተገቢ የሰው ኃይል አለመቅረቡ፤ ሠልጥነው ተመርቀው የወጡ ዜጎችም ሥራ ፈጣሪ አለመሆናቸው” ይጠቀሳል።

ከታችኛው ክፍል ጀምሮ ከንድፈ ሀሳብ የዘለለ ትምህርት የማያገኘው ተማሪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥም ተመሳሳይ ችግር ይገጥመዋል። በተግባር የተደገፈ እውቀትና ክህሎት ባለማግኘቱም ወደማኅበረሰቡ ሲቀላቀል ችግር የሚፈታ አቅምን ይዞና አዳብሮ አይደለም። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ባሳለፍነው ዓመት ተግባራዊ የሆነው የመውጫ ፈተና ነው።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ተፈትነዋል ካላቸው 150 ሺህ ለመመረቅ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎች ውስጥ 40 በመቶ የሚሆኑት ብቻ ፈተናው የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልተው ለመመረቅ ብቁ መሆናቸው ነው። በተለይ ካለፉት ውስጥ 63 በመቶ የሚሆኑት ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሆኑ የግል ትምህርት ቤቶች ቀሪውን 37 በመቶ ብቻ ማስመዝገባቸው ትኩረታችን የቱ ጋር ሊሆን እንደሚገባ ቁልጭ አድርጎ ያስመለከተን ይመስላል።

የሆነው ሆኖ “16 እና ከዚያ በላይ ዓመት እውቀትን ለመገብየት ትምህርት ቤት ሲመላለስ የነበረ በርካታ ሚሊዮን ትውልድ ጥራት ያለው ትምህርት እያገኘ አይደለም” ስንል የሚያስነሳው ጥያቄ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል። ሂደቱ ሀገራዊ ፍላጎትን በትክክል ያላገናዘበ እንደነበር፣ የሙያ ደረጃ በማውጣትና የትብብር ሥልጠናን መተግበር የሚያስችልና ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ሥርዓት አለመዘርጋቱን እንድናስተውል ያስገድደናል። ሀገር ጠንካራ ኢኮኖሚ እንድትገነባ በእውቀት፣ ክህሎትና የማድረግ አቅሙ የዳበረ ትውልድ ልትመራ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ጠንካራ የትምህርት ፖሊሲ እና ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ሊኖሩን ይገባል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግሥት የትምህርት ሥርዓቱን ለማሻሻልና ጥራትን ለማስጠበቅ ቁርጠኝነትን እያሳየ ነው። ለዚህም ፖሊሲን ጨምሮ ልዩ ልዩ የአሠራር ሥርዓቶችን እያሻሻለ ይገኛል። በቀዳሚነት ግን ባሳለፍነው ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ “የትምህርት አሰጣጣችንና ትውልዱ” ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሽፍንፍኑን ገላልጠን ማየት ችለናል።

በቀደመው የትምህርት ሥርዓታችን ያፈራነው ትውልድ የቀረፅነው ተማሪ ውጤት ሲመዘን ከጭድ ቀልሎ ታይቷል። ይህንን ካወቅን ዘንዳ ቀጣይ መሆን የሚገባውን መዘየድ ተገቢ ነው። የኢትዮጵያን የማደግ ፍላጎት፣ ነባራዊ የልማትና እድገት ደረጃ የሚመጥን ትውልድ ለማፍራት የሚያስችል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ቀርጸናል። ይህ ፖለሲና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ግን መሬት ላይ እንዲወርድ ርብርበ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ከዚያ ባለፈ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት እና እየመጣ ባለው ውጤት ማዘንና “ሙሾ” ማውረድ ብቻ ለውጥ ስለማያመጣ በቀጥታ ወደ ተግባራዊ ሥራው መሸጋገር ይኖርብናል። በመሆኑም የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው መሻሻል ገፊ ምክንያት ከሆኑት መርሆች በመነሳት የሚከተለውን ምክረ ሀሳብ ይሰጣል።

የመጀመሪያው ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና ለሁሉም በማዳረስ የግለሰብን አዕምሯዊ አካላዊ፤ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ እንዲሁም መልካም እሴቶችን ማጎልበት እንደሚገባ ነው። የፖሊሲው ዋና ርዕሰ ነገር ለሆነው ለዚህ ቀዳሚ ዓላማ ተፈፃሚነት ደግሞ ሙሉ አቅምን መጠቀም ያስፈልጋል።

በሁለተኛና በመጨረሻ መነሳት ያለበት ቁልፍ ዓላማ “የኢትዮጵያን ባሕል፣ እሴቶች የተገነዘበ ለሀገር አንድነት እድገት የሚሠራ፣ በራሱ የሚተማመንና ሙሉ የሆነ” የተማረ ኃይል እንዲፈጠር በወረቀት ላይ ያስቀመጥነውን ራዕይና እቅድ ተግባራዊ እንዲሆን መሥራት እንደሚያስፈልግ ነው።

ይህንን ማድረግ ስንችል ለሁለትና ሦስት ዓመታት “ጉድ” ያስባለንና ብዙ ጉድለቶች የነበሩበትን የመማር ማስተማር ሥርዓት ከስር መሠረቱ መቀየር ያስችለናል። በመሆኑም ከቁጭት ወጥተን “ለተሻሻለው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተግባራዊነት እንሥራ” የሚለው የዛሬ ርዕሰ ነገር መቋጫችን ይሆናል። ሰላም!

# የኢትዮጵያን መልክ በአንድ ቦታ ከማሳየት ባሻገር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች ያላትን ዕምቅ ሃብት በማስተዋወቁ በኩል ሰፋፊ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። በተለይም አምራችና ሸማችን የሚያገናኙ የተለያዩ የንግድ ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን ጨምሮ በርካታ አገርን፣ ምርቶቿን፣ እምቅ አቅሞቿን፣ ማስተዋወቅና የገበያ ትስስር መፍጠር የሚያስችሉ እውቀትና ቴክኖሎጂን የማስተላለፍ አቅም ያላቸው አውደ ርዕዮችን ማዘጋጀት እየተለመደ መጥቷል። ከሰሞኑም በዓይነቱ ለየት ያለና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ የሚጠበቀው ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ኢንቨስትመንት አውደ ርዕይ በይፋ ተከፍቶ እየተጎበኘ ነው፡፡

ይህ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት አውደ ርዕይ፤ መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ.ም በተከፈተበት ወቅት ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ አሁን ጊዜው ድህነትን የምንታገልበት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት በማውጣት በጋራ የምናለማበት ወቅት ነው ብለዋል፡፡ ኢትዮጵያ የብዙ ውበቶችና ግኝቶች መዳረሻ መሆኗን ጠቅሰው፣ ይህን በማስተዋወቅ እንዲሁም ያለንን አቅም በማውጣት እያንዳንዳችን አገሪቱ ያላትን ሀብት ማየት፣ ማውጣት፣ ማስተዋወቅና ማገልገል ይጠበቅብናል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

በአገር አቀፉ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ኢንቨስትመንት አውደ ርዕይ ላይ ከ100 በላይ በዘርፉ የተሰማሩ ሆቴሎች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የክልል ቱሪዝም ቢሮዎች፣ የሚዲያና የቴክኖሎጂ ተቋማት ፣ በባህል አልባሳት ምርት፣ በሽመና እንዲሁም በሸክላ ሥራ የተሰማሩ የዘርፉ ባለሙያዎች እየተሳተፉ ናቸው። አምራቾቹ ምርቶቻቸውን ለማስተዋወቅ፣ የገበያ ዕድል ለመፍጠርና አንዱ ከሌላው የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የተሻለ ዕድል እንደተፈጠረላቸው ይናገራሉ።

አቶ ሰለሞን ወረደ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች መካከል አንዱ በሆነው በኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት የስጋጃ ባለሙያ ናቸው፡፡ በአውደ ርዕዩ ድርጅቱ መሳተፉ ምርቶቹን ለጎብኚዎች ለማስተዋወቅና ለገበያ ትስስር ትልቅ እድል እንደሚፈጥር ይናገራሉ። በተለይም የድርጅቱ ምርቶች በሙሉ ባህላዊና ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቁ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ከቱሪዝሙ ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ።


እሳቸው እንዳሉት፤ ድርጅቱ በ1957 ዓ.ም በስድስት ሠራተኞች የተቋቋመ ነው፡፡ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የእጅ ሥራ ምርቶችን በመሥራት ለገበያ ያቀርባል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የበርካታ ሙያ ባለቤት በሆኑ ሠራተኞቹ አማካኝነት የተለያዩ ምርቶችን እያመረተ ይገኛል፡፡ ከምርቶቹ መካከልም የቀርከሃ፣ የስጋጃ፣ የሸክላ፣ የስዕልና የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎች ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህን ምርቶች በስፋት ለቱሪስቶች እንደሚያስተዋውቁ ያመላከቱት አቶ ሰለሞን፤ ቱሪስቶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች በሙሉ ምርቶቻቸውን ይዘው በመቅረብ በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር እንደሚፈጥሩ ይናገራሉ፡፡ በአገር ውስጥ ከሚገኙ የድርጅቱ ደንበኞች በተጨማሪ አብዛኛውን ጊዜ የገበያ መዳረሻዎቹ ቱሪስቶች እንደሆኑ ተናግረዋል። ድርጅቱ በትዕዛዝ ተቀብሎ ከሚያመርታቸው ማንኛቸውም ምርቶች በተጨማሪም በራሱ ዲዛይንና ቀለም የተለያዩ ምርቶችን አምርቶ ለገበያ ያቀርባል ይላሉ፡፡

ይሁንና ድርጅቱ ምርቶቹን በስፋት ለማህበረሰቡ ማድረስ አለመቻሉን የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ እንዲህ ያሉ አውደ ርዕዮች ድርጅቱን ከአብዛኛው ማህበረሰቡ ጋር እንደሚያስተዋውቁና የገበያ ዕድል እንደሚፈጥሩም ተናግረዋል፡፡ ድርጅቱ አሁን ካሉት ደንበኞች በተጨማሪ ምርቶቹን በስፋት አምርቶ ለሸማቹ ለማቅረብ እየሠራ እንደሆነ ነው ያስታወቁት።

ድርጅቱ ሥራውን እያሰፋ እንደሚገኝም ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት አያት አደባባይ አካባቢ ከ1000 ካሬ ሜትር በሚበልጥ ቦታ ላይ የማስፋፊያ ስራ እየሰራ



**በኤግቢሽኑ የጌጣጌጥ፣ የባህል አልባሳትና የመሳሰሉት አምራቾች ምርቶቻቸውን እያስተዋወቁ ናቸው፣**

መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚሁ የማምረቻ ቦታ ላይ የተለያዩ ባህላዊና አገር በቀል ምርቶችን ከማምረት ባሻገር በዘርፉ ስልጠና እንደሚሰጥም አስታውቀዋል። ምርቶችን በስፋት በማምረትና በማሰልጠን እስካሁን በስፋት ያልገባባቸውን ገበያዎች እንደሚለቀላቀልም ጠቁመዋል፡፡ ምርቶቹን በአገር ውስጥ ለሚገኙ ሸማቾች ከማድረስ ባለፈ የማምረት አቅሙን በማሳደግ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አቅዶ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ድርጅቱ ምርቶቹን በስፋት እያቀረበ ያለው ለተለያዩ ዘመናዊና የባህል ሆቴሎች እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ ባህላዊ ከሆኑ ሆቴሎች ጋር የገበያ ትስስር ፈጥሮ ምርቶቹን እያቀረበ ይገኛል ብለዋል፡፡ ዮድ አቢሲኒያ፣ ቃተኛና የመሳሰሉት ባህላዊ ይዘት ያላቸው ሆቴሎች ደንበኞቹ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ ሆቴሎቹ ከቤት አሰራራቸው ጀምሮ ባህላዊ ይዘት ያላቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በቤት ውስጥ ያሉ ቁሳቁስ ወንበርና ጠረጴዛን ጨምሮ የሸክላ ሥራ፣ የስጋጃ ሥራ፣ የቀርከሃ ሥራ፣ በተለያዩ ስዕሎችና መጋረጃዎቹ ጭምር በኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት ምርት የተንቆጠቆጡ መሆናቸውንም አብራርተዋል፡፡

የምርቶቹ ቋሚ ደንበኛ ከሆኑ ሆቴሎች በተጨማሪ ጎንደርና ባህርዳር በሚገኙ ሱቆቹ ምርቶቹን ለገበያ እያቀረበ መሆኑንም አቶ ሰለሞን ተናግረው፣ በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ማለትም በመስቀል አደባባይ፣ ዋቢሸበሌ፣ በሂልተን፣ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ፣ 22 አካባቢና አያት አደባባይ በማምረቻ ሥፍራው በሚገኙ መሸጫ ሱቆች ጭምር ምርቶቹን ለገበያ እያቀረበ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ባህላዊ ቁሳቁሱ አሁን አሁን ተፈላጊነታቸው እየጨመረ መምጣቱንም አመልክተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት የሸክላ ምርቶቹን ከአራት የአፈር አይነቶች ውህድ ያመርታል ፡፡ ከምርቶቹ መካከልም የከትፎ ማቅረቢያ ጣባ፣ ጀበና፣ የሻማ ማብሪያ፣ ድስቶች፣ የላዛኛ ማቅረቢያ ይጠቀሳሉ፡፡ የሸክላ ሥራዎቹ ጥራት ያላቸውና በገበያው እጅግ ተፈላጊ መሆናቸውን አመልክተው፣ ለሸክላ ሥራ ጥራት ዋናው የጭቃው ዝግጅት እንደሆነም አስረድተዋል።

የስጋጃ ምርቶቹ ከበግ ጸጉር ይሰሩ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሰለሞን፤ የበግ ጸጉሩን ጠረን በአሁኑ ወቅት ደንበኞች አይፈልጉትም ብለዋል፡፡ የበግ ጸጉሩ በክር ተቀይሮ እንደሚሰራም ገልጸዋል። ክሩ በተለያዩ ቀለማት ተነክሮ ደንበኞች በሚፈለጉት ዲዛይን እንደሚሰራ፣ ድርጅቶችም በድርጅታቸው ሎጎ እንደሚያሰሩ ተናግረዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ቀርከሃም እንዲሁ ለተለያዩ ምርቶች ይውላል፡፡ ቀርከሃ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት ቢኖርም በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም፡፡ ድርጅቱ ቀርከሃን ለመብራት ጌጥ፣ ለፍራፍሬ ማቅረቢያ፣ ለወንበር፣ ለጠረጴዛና ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ አድርጎ እያመረተ ለገበያ ያቀርባል፡፡ ድርጅቱ ኢትዮጵያን መግለጽ የሚችሉ የተለያዩ ስዕሎችን አምርቶ ለገበያ የሚያቀርብ ሲሆን፤ ለዚህ ሥራም የድርጅቱ ሰዓሊዎች ትልቅ አበርክቶ አላቸው፡፡

ድርጅቱ በአጠቃላይ በአገር ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁስን ብቻ በመጠቀም ባህላዊ ምርቶችን እያመረተ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ገበያዎቹ የውጭ አገር ቱሪስት እና ባህላዊ ሆቴሎች ናቸው፡፡ ይሁንና አሁን አሁን የአገር ውስጥ ሸማቾችም ወደ ባህላዊ ምርቶቹ እየመጣ በመሆኑ ምርቶቹን በስፋት አምርቶ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አስፈላጊውን ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በእነዚህ ምርቶች አገርን ማስተዋወቅና የገቢ ምንጭን ማሳደግ እንደሚቻል አቶ ሰሎሞን ተናግረዋል። ለዚህም በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በስፋት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅትም ፍላጎት ያላቸውን በሙሉ በተለያየ ዘርፍ ለማሰልጠን መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

በአውደ ርዕዩ ላይ የተለያዩ ጌጣ ጌጦችን ይዘው ከቀረቡት መካከል የእንጦጦ ዕደ ጥበብ ድርጅት አንዱ ነው፡፡ እንጦጦ ዕደ ጥበብ 200 የሚደርሱና በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የነበሩና ከማህበረሰቡ ተገልለው የቆዩ ሴቶችን አሰባስቦ ወደ ሥራ ማሰማራት የቻለ ሲሆን፤ ጌጣ ጌጦችን፣ ሰፌዶችን፣ መሶቦችንና የቆዳ ውጤቶችን የሚያመርት ነው ፡፡

የድርጅቱ የማርኬቲንግ ባለሙያዋ ወይዘሪት ይዲዲያ ሰለሞን እንዳለችው ፤ ለተለያዩ ፕሮግራሞች መዋቢያነት የሚያገለግሉ የአንገት፣ የጆሮ፣ የእጅና እግር ላይ የሚውሉ የተለያዩ ጌጣ ያመርታል፡፡ ጌጣ ጌጦቹ የሚሰሩትም ከጥይት ቀለሃ ሲሆን፣ ጌጣ ጌጦቹን ከቀለሃው ለመሥራት ምንም አይነት ማሽን ጥቅም ላይ አይውልም፤ ሙሉ ለሙሉ በእጅ ነው የሚሰሩት፡፡

ምርቶቹን በአብዛኛው የሚገዙት ቱሪስቶች እንደሆኑ የጠቀሰችው ወይዘሪት ይዲዲያ፤ ወደ አገር ውስጥ ለሚመጡ ቱሪስቶች ምርቶቹን በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ሱቆቻቸው እንደሚያቀርቡ ገልጻለች፡፡ በአገር ውስጥ ካለው ገበያ በተጨማሪ አሜሪካ፣ ካናዳና በሌሎች አገራትም እንዲሁ ጌጣ ጌጦቹን በመላክ ለገበያ እንደሚያቀርቡ ተናግራለች። በአገር ውስጥም በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት አብዛኛው ሰው ዘንድ መድረስ እየቻሉ እንደሆነ አስረድታለች፡፡ እንደዚህ አይነት ለህዝብ ክፍት የሆኑ አውደ ርዕዮች የገበያ ትስስር ለመፍጠርና ሥራዎቻቸውን ለማስተዋወቅ እጅግ ጠቃሚ መሆናቸውንም ወይዘሪት ይዲዲያ ተናግራለች፡፡

የቱሪዝም ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ አለማየሁ ጌታቸው በበኩላቸው እንዳሉት፤ በአውደ ርዕዩ ከ100 በላይ ተቋማት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ አውደ ርዕዩ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን፣ ምርትና አገልግሎታቸውን ከማስተዋወቅ ባለፈ የገበያ ትስስር የመፍጠርና የልምድ ልውውጥ የማድረግ አጋጣሚንም ይፈጥራል፡፡

አውደ ርዕዩ በይዘቱ ለየት ያለና ኢትዮጵያን መግለጽ የሚችል እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አለማየሁ፣ አገልግሎት ሰጪ ሆቴሎች በአውደ ርዕዩ ተሳታፊ በመሆን አገልግሎታቸውን እያስተዋወቁ መሆናቸውንም ተናግረዋል፡፡ በከተማ ውስጥ የሚገኙ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ቁጥራቸው በርካታ እንደመሆናቸው በተራ እየገቡ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እየተደረገ መሆኑንም ተናግረዋል። ሌሎች ሽመናን ጨምሮ የተለያዩ ባህላዊ የሆኑ ቁሳቁስን የሚያመርቱ ድርጅቶችም በአውደ ርዕዩ ተሳታፊ በመሆን ምርቶቻቸውን እያስተዋወቁና የገበያ ትስስርም እየፈጠሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የቱሪዝም ሚኒስቴር ይህን አውደ ርዕይ ያዘጋጀበት ዋና ዓላማ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማነቃቃት፣ በዘርፉ በአንድም ሆነ በሌላ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የተሳሰሩ አካላት እንዲተዋወቁ ማድረግ፣ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችም እንደዚሁ በአንድ ቦታ የኢትዮጵያን መልክ እንዲያዩና ወደ ሥፍራው የመሄድ ፍላጎታቸው እንዲጨምር ለማድረግ ነው። በቱሪዝም ዘርፍ ያለውን የኢንቨስትመንት እድል በማሳየት ኢንቨስትመንቱ እንዲጨምር ማድረግ፣ ጎብኚዎች ከሚጎኙት ነገር ተነስተው የራሳቸውን የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዲፈልጉ ማስቻል፣ የፈጠራ ክህሎት እንዲዳብርና እንዲጨምር ዕድል መፍጠር፣ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶች እንዲፈጠሩ ማድረግ እንዲሁም ጎን ለጎን ያሉትን መልካም ነገሮች አበርክቶ ለመጠቀምና በተመሳሳይ በጋራ የመወያትና የመመካከር ዕድል በመፍጠር ችግሮችን መፍታትም ሌሎች የአውደ ርእዩ አላማዎች ናቸው፡፡

በሽመና ሥራ የተሰማሩ ባለሙያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ባህላዊ ቁሳቁስን የሚያመርቱ ድርጅቶች በአውደ ርእዩ እየተሳተፉ መሆናቸውን አመልክተው፣ እነዚህ ድርጅቶች ለቱሪዝሙ ያላቸውን የላቀ ፋይዳ በአውደ ርዕዩ ማሳየት እየተቻለ መሆኑን አቶ አለማየሁ አስታወቀዋል፡፡ እያንዳንዱ ቱሪስት በቦታው ሲገኝ ወደ አገሩ ይዞት የሚሄደውና ኢትዮጵያን ለማስታወስ የሚያስችለውን ከፎቶና ከቪዲዮ ባሻገር የተለያዩ ቁሳቁስን ይፈልጋል ያሉት ስራ አስፈጻሚው፣ ለዚህም በባህላዊ ቁሳቁስ ማምረት ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች ኢትዮጵያን የሚገልጹ በርካታ ምርቶችን ይዘው መቅረባቸውን ተናግረዋል፡፡ ሁሉም ነገር በአንድ ቦታ ላይ ተከማችቶ የቀረበበትን ይህን አውደ ርዕይ ሁሉም ሰው እንዲጎበኝ በማለት ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

አውደ ርዕዩ እስከ ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ክፍት የሥራ ቀያሪ ማስታወቂያዎች

**ዋሰልኝ አየለ**

በ2010 ዓ.ም የለውጡ ሰሞን ይመስለኛል። በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮምኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር የነበሩት፤ በኋላም የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሆነው የነበሩት ዶክተር ጌታቸው ድንቁ በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሁኔታ ላይ ጽሑፍ አቅርበው ነበር፡፡ በቅርስ ጥናት ጥበቃ ባለሥልጣን አዳራሽ በተደረገው በዚያ ውይይት ብዙ ሀሳቦች የተነሱ ቢሆንም፤ ዶክተር ጌታቸው ያነሱት አንድ ነጥብ ግን አሁን ድረስ አይረሳኝም፡፡

የዶክተር ጌታቸው ሀሳብ ሲጠቃለል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ችግር የባለሙያዎች አንድ ተቋም ውስጥ አለመቆየት ነው፡፡ ከዚህም ሲከፋ ደግሞ ሙያቸውን ቀይረው በሌላ የተሻለ ቢዝነስ ሊያስገኝ በሚችል ነገር የሚሰማሩ መሆናቸው ነው፡፡ የትኛው የተሻለ ይከፍላል በሚል ከተቋም ተቋም መዘዋወር የተለመደ እና መደበኛ አሰራር ሆኗል፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሙያው ተገቢውን ክብር አያገኝም፤ የባለሙያዎቹ ፍላጎትም ከሙያው ይልቅ የተሻለ ክፍያ ማግኘትን ነው፡፡

እርሳቸው ምሳሌ አድርገው የጠቀሱት የጋዜጠኝነትን ሙያ ነው፡፡ የሠለጠኑ አገራት ውስጥ ያሉ ዓለም አቀፍ ዝና ያላቸውን የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትና ጋዜጠኞችን ምሳሌ ሲጠቅሱ፤ ከ30 ዓመት በታች የሆነ ጋዜጠኛ አይገኝም፡፡ በአንድ መገናኛ ብዙኃን ውስጥ ለረጅም ዓመታት ይቆያሉ፡፡ በአንድ በሆነ ነገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁ በዚያው ነው የሚቀጥሉት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከ30 ዓመት በላይ የሆኑ ጋዜጠኞችን ማግኘት ዕድሉ ጠባብ ነው፤ ምክንያቱም በሙያው ትንሽ ከሰሩ ወደሌላ ዘርፍ ይሄዳሉ፤ ቢዝነስ የሚያስገኝ ነገር ፍለጋ ይሄዳሉ፡፡

የዶክተር ጌታቸውን ጥናታዊ ጽሑፍ ምሳሌ ያነሳሁት ለአንድ ሙያ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከሄድን ኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ሙያዎች ውስጥ ተመሳሳይ ችግር ነው ያለው፡፡ ከተቋም ተቋም፣ ከሙያ ሙያ መቀያየር የተለመደ ነው፡፡ እንዲያውም አንድ መስሪያ ቤት ውስጥ መቆየት እንደ ስንፍና ነው የሚታየው፡፡ እየቀያየሩ ማየት እንደ ፋሽን ተደርጓል፡፡ ይሄ ማለት ዋናው ጉዳይ የሙያው ሳይሆን ባለሙያው የሚያገኘው ገንዘብ ሆኗል ማለት ነው፡፡

የሚወጡ ክፍት የሥራ ማስታወቂያዎችን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ ለሥራ ፈላጊዎች ሳይሆን ለሥራ ቀያሪዎች የሚወጡ ናቸው፡፡ ክፍት የሥራ ማስታወቂያው ላይ የሚገለጹት ክፍት የሥራ መደቦች በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ይሄ ማለት ክፍት የሥራ ማስታወቂያውን ካወጣው ተቋም ውስጥ በዚያ መደብ የለቀቁ ሠራተኞች አሉ ማለት ነው፡፡ ከተቋም ወደ ተቋም እንዲህ አይነት ዝውውር ሲበዛ ሁሉም ተቋማት ለክፍት የሥራ መደቦች ማስታወቂያ ያወጣሉ ማለት ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሥራ ቀያሪዎች ራሱ ይጸጸታሉ፡፡ አንድ ተቋም ደሞዝ ጨመረ ሲባል ወደዚያ ተቋም ይሄዳሉ፡፡ ልክ ሄደው እንደተቀጠሩ ያ የለቀቁት ተቋም ደግሞ አዲስ ከገቡበት የተሻለ አድርጎ ይጨምራል፤ ደግሞ እንደገና ቀልባቸው ወደዚያ ያማትራል፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ የባለሙያው ትኩረት ሙያው ላይ ሳይሆን የተቋማትን የደሞዝና ጥቅማጥቅም ስኬል ማጥናት ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ሥራ እና ሙያ ይበደላል ማለት ነው፡፡ ሥራ እና ሙያ እንዴት እንደሚበደል ማሳያዎችን እንጥቀስ፡፡ ይህን ለመታዘብ በተለይም የጋዜጠኝነት ሙያ ምቹ ነው፡፡

ወደ አንድ ተቋም መረጃ ለማግኘት እንደውላለን፡፡ ጉዳዩ ይመለከተዋል የሚባለውን ባለሙያ ያገናኙናል። ባለሙያው ሲጠየቁ፤ ‹‹አዲስ የገባሁ ስለሆንኩ ገና ነኝ›› ይላሉ፡፡ ይለምዳሉ ተብሎ ሲጠበቅ ደግሞ፤ ምናልባትም ተቀይረው ይገኙ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ተቋም ውስጥ የሆነ ዘርፍ ላይ ባለሙያ አሉ እንበል፡፡ ባለሙያው በአንድ ወቅት መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ያንኑ ጉዳይ ምን ላይ እንደደረሰ ለመጠየቅ ሲደወል ‹‹እኔ አይደለሁም! ሌላ ሰው ነው!›› በማለት ከዚያ ሙያ እንደለቀቁ ይናገራሉ።አዲስ የገባው ደግሞ ገና አልተላመደምና መረጃው የለኝም ሊል ይችላል፡፡

ይሄ ነገር ከታች ባሉ ባለሙያዎች ብቻ የሚታይ ችግር አይደለም፡፡ በከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ ራሱ በተደጋጋሚ የምናየው ነው፡፡ በሌሎች አገራት የአንድ ሚኒስትር ስም ከአገሪቱ ጋር ብራንድ መስሎ ይቆያል፡፡ ለምሳሌ የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲባል ሰርጌይ ላቭሮቭ የሚለው ቃል ቶሎ ወደ አዕምሮ ይመጣል፡፡ የግብጽ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲባል ሳሚ ሹክሪህ የሚለው ስም ቶሎ ይታወሳል፡፡ በእርግጥ ይህ የሆነው ለረጅም ዓመታት መቆየታቸው ብቻ ሳይሆን ስማቸው የሚጠራበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ ነው፡፡

እንደ ቢቢሲ፣ አልጀዚራ፣ ሲ ኤን ኤን፣ ፍራንስ 24... የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንን ልብ ብላችሁ ይሆናል፡፡ ጋዜጠኞቻቸው ከረጅም ዓመታት በፊት የነበሩ ናቸው፡፡ በዚያ ሙያ ላይ ልምድና በርካታ ገጠመኞችን አካብተዋል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች ብዙ ልምድ ስላላቸው ለተቋሙም ሆነ ለአገራቸው ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ ማለት ነው፡፡

ለረጅም ዓመታት የሚቆይባቸው ሙያዎች ምናልባት መምሕርነት እና ሕክምና ይመስሉኛል። መምሕርነትም ቢሆን ከግል ወደ መንግሥት፣ ከመንግሥት ወደ ግል ትምህርት ቤቶች መቀያየር አለበት፡፡ ከዚያ ውጭ ያሉት ሙያዎች ግን መቀያየር ዋና መገለጫቸው ሆኗል፡፡ እንዲያውም ጓደኛሞች ሲገናኙ ‹‹አሁን የት ነህ?›› ተባብለው ይጠያየቃሉ፡፡ መቀየር እንዳለበት ይታመናል ማለት ነው፡፡ ‹‹አሁንም እዚያው ነህ?›› በማለት አለመቀየሬን በግርምት ይታዘባሉ፡፡ ይሄ ነገር ልማድ ሆነና አለመቀየር እንዲያውም እንደ ስንፍና ሊታይ ነው፡፡

በእርግጥ እነዚህ ነገሮች የሆኑበት ምክንያት የኑሮ ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አገራችን አሁንም ድሃ ናት፡፡ ተቋማት ለባለሙያዎቻቸው በቂ የሚባል ደሞዝና ጥቅማጥቅም ሊከፍሉ አይችሉም፡፡ በዚያ ላይ ተመሳሳይ የሆነ አሰራር የለም፡፡ በተመሳሳይ ሙያ የተለያየ ክፍያ ነው ያለው፡፡ ስለዚህ ባለሙያው ያንኑ ሥራ እየሰራ ከሙያ እኩዮቹ በታች ሲከፈለው ቅያሪ መፈለጉ አይቀሬ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እየሰራ ያለበት ሙያው ለመኖር በቂ የሆነ ክፍያ የማያገኝበት ከሆነ ሌላ የቢዝነስ ሥራ ይሰራል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ጎበዝ የሚባል እና ተማሪዎች የሚወዱት የፊዚክስ መምህር አለ እንበል፡፡ ይህ መምህር በሚከፈለው ደሞዝ ቤተሰቡን ማስተዳደር ካልቻለ እና ሌላ የቢዝነስ አማራጭ ካገኘ መምህርነቱን ይተወዋል። አለበለዚያ ደግሞ ከመምህርነቱ ጋር ለማስኬድ ይሞክራል፤ ይህ ደግሞ ሙያውን ይበድላል ማለት ነው፡፡

ይህ የባለሙያ መሥሪያ ቤት መቀያየር ሙያን መበደል ነው፡፡ ሥራን እና ደንበኛን ማጉላላት ነው። ስለዚህ እንደ ባለሙያም፣ እንደ ዜጋም፣ እንደ መንግሥትም ሊታሰብበት ይገባል!

# ዓለም አቀፍ


## የአየር ንብረት ለውጥ ለወባ በሽታ መስፋፋት ዋነኛው ምክንያት ሁኗል

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በወባ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር ዋነኛው ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ መሆኑ ተገልጿል። እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ዘገባ ከሆነ እኤአ 2021 ከዓለም ሕዝብ ግማሽ ያህሉ ለወባ የተጋለጠ ሲሆን፤ በዚሁ ዓመት የቫይረሱ ተጠቂዎች ቁጥር 247 ሚሊዮን ደርሷል።

ከእነዚህም ውስጥ 619 ሺህ ያህሉ ሕይወታቸው አልፏል። ድርጅቱ አፍሪካ በዓለም ትልቁን ድርሻ እንደምትይዝ ያምናል። በ2021 በበሽታው የተያዙ 95 በመቶ ያህሉ በአሕጉሪቱ እንደሚገኙ ተጠቅሷል። የአየር ንብረት ለውጥ እና የዝናብ ሁኔታ ለውጥ ወባ ተሸካሚ ትንኞች መራባት እና መስፋፋት እንዲጨምር ከማድረግ በተጨማሪም አዳዲስ አካባቢዎች መታየት፣ ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት መቻላቸው ስፋቱን ይጨምራል።

የዓለም የጤና ድርጅት አስቀድሞ ምርመራ ማድረግን ይመክራል። ምክንያቱም ሕክምናው ከባድ ሕመም እና ሞትን በመከላከሉ እንዲሁም የወባ ስርጭትን ስለሚገድብ ነው። አብዛኛው የወባ ተጠቂነት እና ሞት እንደ አፍሪካ ባሉ ታዳጊ ሀገራት የሚከሰተው በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ነው።

የወባ ትንኞች በአፍሪካ አየር ንብረት ውስጥ በሕይወት ሊቆዩ እና ሊራቡ ስለሚችሉ፣ በተጨማሪም የጤና በጀት አነስተኛ መሆን እና ቀጣይነት ያለው የህብት ብዝበዛ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ሞቃታማ አየር ንብረት ምግብ፣ ውሃ እና ተላላፊ በሽታዎች እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ይህም ቀደም ሲል ያልተጋለጡ ሰዎች ላይ በሽታዎችን በማምጣት እንዲሁም በዓለም አቀፍ የሕብረተሰብ ጤና ላይ ለአስርተ ዓመታት የተመዘገበውን እድገት ያወርዳል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።



## ፑቲን የሩሲያና ቻይና «ገደብ የለሽ» ትብብርን ለማጠናከር ወደ ቻይና አምርተዋል

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከቻይናው አቻቸው ሺ ጂንፒንግ ጋር ለመምከር ትናትና ቤጂንግ ገብተዋል። ፕሬዚዳንት ፑቲን እስከ ዛሬ በሚቀጥለው 3ኛው የአንድ ቀበቶ አንድ መንገድ (ቤልት ኤንድ ሮድ) ፎረም ላይ ይሳተፋሉ።

የዩክሬኑ ጦርነት በቀጠለበት ወቅት ፑቲን ቤጂንግ መግባታቸው የቻይና እና ሩሲያን በመተማመን ላይ የተመሰረተና “ገደብ አልባ” ትብብር ያሳያል ተብሏል። የዓለማቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት (አይሲሲ) በመጋቢት ወር በፑቲን ላይ የእስር ማዘዣ ካወጣ በኋላ የትናትናው የቤጂንግ ጉዞ ሁለተኛው የውጭ ሀገር ጉብኝታቸው ነው ተብሏል።



ፑቲን በጥቅምት ወር መግቢያ በቀድሞዋ የሶቪየት ሕብረት አካል ኪርጊስታን ጉብኝት ማድረጋቸው

የሚታወስ ነው። ቻይናም ሆነች ኪርጊስታን የአይሲሲ ፈራሚ አባል አለመሆናቸውን የሚጠቅሰው ሬውተርስ፥ ትልቅ ዜና የሚሆነው ፑቲን ወደ አይሲሲ አባል ሀገራት ጉብኝት ሲያመሩ ነው ይላል።

የእስር ማዘዣው በወጣ በቀናት ልዩነት ወደ ሞስኮ የዘለቁት ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ ፑቲን ሀገራቸውን እንዲጎበኙ እና በ3ኛው የአንድ ቀበቶ አንድ መንገድ ፎረም እንዲካፈሉ ያቀረቡላቸውን ጥሪ ተቀብለው ቤጂንግ ገብተዋል። ፑቲን በዛሬው እለት በፎረሙ ላይ ንግግር እንደሚያደርጉና ከፕሬዚዳንት ሺ ጋርም የሁለትዮሽ ምክክር እንደሚያደርጉ ተገልጿል።

የሩሲያ እና ዩክሬን ከተጀመረ ወዲህ ሞስኮ ከቤጂንግ ጋር ይበልጥ ግንኙነቷን አጠንክራለች። ሩሲያ በየቀኑ ከ2 ሚሊየን በርሜል በላይ ነዳጅ ወደ ቻይና የምትልክ ሲሆን፥ ሁለተኛውን የተፈጥሮ ጋዝ ማስተላለፊያ መስመርም ለመገንባት አቅዳለች። ቻይና የሩሲያን ነዳጅ በመግዛቷ 10 ቢሊዮን ዶላር አተረፍኩ ማለቷም የሚታወስ ነው፡፡

ከፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር ወደ ቤጂንግ ያመሩት የሩሲያ ግዙፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ጋዝፕሮም እና ሮስኔፍት የስራ ኃላፊዎች ሁለተኛው የተፈጥሮ ጋዝ ማስተላለፊያ ስለሚገነባበት ሁኔታ ይመክራሉ መባሉን አል ዐይን ዘግቧል፡፡

# ባለውለታዎቻችን

## ፋና ወጊዋ ሴት የኪነ ሕንፃ ባለሙያ

ክብረአብ በላቸው



ምሁር ለሚለው ቃል አቻ እንግሊዝኛ ትርጉሙ ኢንተለክቹዋል የሚለው ፍቺ ነው። የአማርኛ ቋንቋ ደግሞ ምሁር የሚለውን ቃል ከፍተኛ የሆነ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ያለው ብሎ ይተነትነዋል ወይም ትርጉም ይሰጠዋል። በትምህርት የሚገኘው ዕውቀት በተግባር ለውጥና መሻሻል ካላመጣ ትምህርት መማሩና ማስተማሩ በራሱ ትርጉም የለውም ይላሉ ብዙዎች። የአንድ ሰው በትምህርት የተገኘ ዕውቀት ፋይዳ የሚኖረው በራስና በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ሲያስችል እንደሆነ በመግለፅ።

በተለያዩ ወቅቶች እና ቦታዎች መታዘብ እንደምንችለው ‹ምሁር› የሚለው ስያሜ በሀገራችን ተለጥጦ ፊደል የቆጠረን ሁሉ አካትቶ ይዟል፡፡ እዚህ ላይ በመጀመሪያ የምናገኘው ችግር ምሁርን (Intellectual) ከባለሙያ (Professional) መደባለቅን ነው። ባለሙያ የሚለውን ማዕረግ ከሳቴ ብርሐን የአማርኛ መዝገበ ቃላት «ሥራን ዐዋቂ መኾን ልዩ ልዩ የትምህርት ሥራን የእጅ ሥራ ጥበብን ማወቅ ወይንም የአንድ ቀን ሥራን ሠርቶ ደመወዝን ማግኘት።» በማለት የተወሰነ ስራን መስራት እና ምንዳን እንደ ምላሽ ማግኘት (Quid Pro Quo) በማለት ያቀርበዋል፡፡ ምሁር የሚለውን ስያሜ ደግሞ ‹ከፍተኛ የሆነ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ያለው፤ ሊቅ የተማረ በኹሉ ምሉ ትምህርት ያለው ሰው› ብሎ ሰፊ ደርዝ በማስያዝ ምሁርነት ከፍ ያለ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

የምሁር ዕውቀት የሰዎችን ኑሮና አኗኗር ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻሻል የራሱን አስተዋፅዖ ማበርከት እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በእያንዳንዱ የዕውቀት ዘርፍ የሚደረግ ጥናትና ምርምር የሰዎችን ሕይወት በማሻሻል ላይ ማዕከል ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ፣ አንድ ሰው በትክክል “ምሁር” ለመባል ብቁ የሚሆነው ዕውቀቱን ከራሱ አልፎ በሌሎች ሕይወት ላይ ለውጥና መሻሻል ለማምጣት የሚጠቀምበት ከሆነ ነው፡፡ ምሁርነትም ከዚህ አንፃር ታይቶና ተመዝኖ የሚሰጥ ክብር እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

ስለዚህ ምሁር ማለት በልምድ፣ በትምህርትና በልዩ ልዩ መንገድ ያገኛቸውን ማስተዋሎችና ዕውቀት በሐሳብ መልክ ለኅብረተሰቡ የሚያቀርብ ሰው ነው። ለዚህ ቃል ብቁ ሆነው የተገኙ እና የሀገራቸውን ስም ያስጠሩ ዕንቁ ኢትዮጵያን አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ወይዘሮ ምንትዋብ አዱኛ አንዷ ናቸው።

አብዛኞች እንደዋዛ ጥለዋት በሚለይዋት ዓለም በተቃራኒው ጥቂቶች ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የሚተርፍ አስተዋጽኦ አበርክተው ማለፉ ይሳካላቸዋል። በሚያልፍ ዕድሜ የማያልፍ ሥራ ሠርተው ስማቸው ሲወሳ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ከቀናት በፊት ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት የመጀመሪያዋ ሴት ኢትዮጵያዊ አርክቴክት ወይዘሮ ምንትዋብ አዱኛ አንዷ ናቸው። ባለዕውቀት ብስለት ከጥበብ ጋር ከሰመረላቸው ለኢትዮጵያ የኪነ ሕንፃ ብዙ ከሰሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ናቸው ወይዘሮ ምንትዋብ።

ወይዘሮ ምንትዋብ አዱኛ ከአባታቸው ከአቶ አዱኛ ካሳ እና ከእናታቸው ሴት አርበኛ ወይዘሮ ሙሉእመቤት ኃይለሥላሴ በታሕሳስ ወር በዕለተ ዕሁድ በቀን 27 ቀን 1931 ዓ.ም በኬንያ ናይሮቢ ከተማ ተወለዱ። ወይዘሮ ምንትዋብ አዱኛ በኬንያ ናይሮቢ ብዙም ሳይቆዩ ከወላጆቻቸው እና ከታላቅ ወንድማቸው ጋር በልጅነታቸው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመልሰው በሐረር ከተማ ነው ያደጉት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ሀረር በየሺ እመቤት የአዳሪ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።

በእሳቸው ትውልድ ለሴት ልጅ የማይታሰብ የሚባለውን የትምህርት ዕድል አግኝተው የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን፥ እንዲሁም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪያቸውንም በቡልጋሪያ ሀገር በሶፊያ ከተማ የተማሩት ወይዘሮ ምንትዋብ በሪጅናል ፕላኒንግ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የሠሩ ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ሴት ነበሩ።

አርክቴክት ምንትዋብ፥ ለሀገራ ኢትዮጵያ ምናልባትም ለአፍሪካ ብሎም ለመላው የጥቁር ሴቶች የመጀመሪያዋ ፋና ወጊ ሴት የስነ ሕንጻ ንድፍ ባለሙያ ናቸው። አርክቴክት ምንትዋብ አዱኛ ወደ ሐገራቸዉ ኢትዮጵያ ተመልሰው ከማገልገላቸው በፊት በአውሮፓ በተለይም በጀርመን ሐገር ለአመታት በሙያቸው መስራት የቻሉ ጥቁር ሴት ኢትዮጵያዊ ነበሩ።

በወቅቱ ምዕራብ ጀርመን በሚባለው በተለይም በሙኒክ ከተማ ከሌሎች የሙያ አጋሮቻቸው ጋር በቡድን እንዲሁም በግላቸው አፓርትመንቶችን፤ ልዩ ልዩ መኖሪያዎችን፥ የሕጻናት መዋያዎችን፥ ሌሎች የተለያዩ አገልግሎት ያላቸውን ግንባታ ንድፎችን ሠርተዋል። ከነዚህም ውስጥ የጀርመን ሙኒክ ኦሎምፒክ የተካሔደበት ስታዲየም ንድፍ ስራ የነበራቸው ተሳትፎ በቀደምትነት ተጠቃሽ ነው፡፡

ወይዘሮ ምንትዋብ ምንም እንኳ በዘን ወቅቱ የዶክትሬት ድግሪያቸውን ትምህርት ለመቀጠል ቢያስቡም ከወላጆቻቸው ትዳር እንዲመሰርቱ ስለተነገራቸው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመልሰው ትዳር መስርተው አንድ ሴትና አንድ ወንድ ልጅ ወልደው ማሳደግና ለትልቅ ቁም ነገር ማብቃት ችለዋል።

አርክቴክት ምንትዋብ አዱኛ በትምህርትና በልምድ ያካበቱትን እውቀት ወደሀገራቸው ይዘው በመምጣት ከሀይለ ስላሴ ዘመን እስከ ኢሕአዴግ ዘመን ድረስ በውጭ ድርጅቶች፥ በመንግሥት መስሪያ ቤቶችና በግላቸው በበጎ ፈቃደኝነትና በቅጥር በልዩ ልዩ የኃላፊነት ደረጃ ለአስርት ዓመታት አገልግለዋል።

በዘመኑ ከሰሯቸው በቀደምነት ከሚጠቀሱት ሥራዎች መካከል የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ የአሁኑ የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ንድፍ ስራ ቡድን አባልነት፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው የሚገኘው የኬኔዲ ቤተመጻሕፍት የማንበቢያ ቦታዎች ነዳፊነት እና በከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስትር መስሪያ ቤት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር የአርክቴክቸር ባለሞያነት ሀገራቸውን በትጋት አገልግለዋል።

ለ German Relief Operation እና Norwegian Save the Children በበጎ ፈቃደኝነት ለ Pan African Housing Group ለመቀሌ የልጆች መንደር ንድፍ ስራ የቡድን ተሳትፎ፣ በዘመነ ደርግ የሕጻናት አምባ ንድፍ ስራ እና አማካሪነት በገጠር ግብርና ቦታ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የአርዳይታ ተቋም ግቢ መልክዓ ምድር ዲዛይነር እና የግንባታ ሱፐርቫይዘር፣ በብሔራዊ መሐንዲሶች እና ኮንትራክተሮች ድርጅት በፕሮግራም እና ቴክኒክ ክፍል ልዩ ልዩ የኃላፊነት ስራዎች ወይዘሮ ምንትዋብ ከሰሯቸው በዋናነት ከሚጠቀሱት ስራዎቻቸው መካከል ናቸው።

በአንድ ወቅት ወይዘሮ ምንትዋብ ከአንድ የሕትመት ሚዲያ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዴት ወደዚህ የኪነ ሕንፃ/አርክቴክቸር/ ሙያ እንደገቡ ሲናገሩ፤ በእርሳቸው ፍላጎት የገቡበት እንደሆነና አጋጣሚ ሆኖ ብዙ ጊዜ አስተዳደጋቸው ከወንዶች ጋር ስለነበር የዚህ ተፅዕኖ ወደዚህ ሙያ እንዲገቡ ምክንያት እንደሆናቸው ተናግረው ነበር።

``ባለኝ እውቀት ሀገሬን እንዳሰብኩት ማገልገል አልቻልኩም'' የሚሉት ወይዘሮ ምንትዋብ የዚህ ምክንያትም የመጀመሪያው ሴት የመሆን ፈተና በወቅቱ የሴት አርክቴክት ስላልነበር ድጋፍ ማግኘት አለመቻላቸው እንደሆነ ተነግረው ነበር፤ በአንድ ወቅት የተሳካ ስራ ብለው የሰሩት የኪነ ሕንፃ ዲዛይን ሥራ በአንድ ግለሰብ መቀደዱ ተስፋ አስቆራጭ እንደነበርና ለሀገራቸው ባሰቡት ልክ ሥራ መስራት እንዳይችሉ እንቅፋት የሆነባቸው እንደነበር ገልፀው ነበር።

በቡልጋሪያ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ሆነው ለእረፍት ወደ አዲስ አበባ በሚመለሱበት ወቅት ወይዘሮ ምንትዋብ የቡልጋሪያን ቋንቋ መናገር በመቻላቸው በነበራቸው ትውውቅ በሕንፃ ኮሌጅ መምህር የነበረ ቡልጋሪያዊ አርክቴክት በእርሱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እየጠራቸው የመጀመሪያዋ ሴት አርክቴክት እያለ ለሌሎች ተማሪዎች ያስተዋወቃቸው ነበር፡፡ ወይዘሮ ምንትዋብ ይህ ሲሆን ለሌሎች ምሳሌ በመሆናቸው ደስ ይላቸው እንደነበረም ገልፀው ነበር።

በኢትዮጵያ ብዙ ሴቶች የእርሳቸውን ሙያ ጨምሮ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተምረውና ተሰማርተው ውጤታማ መሆናቸው ደስ የሚል እንደሆነ ከአንድ ሚዲያ ጋር በነበራቸው ቆይታ የተነገሩት ወይዘሮ ምንትዋብ፤ በትምህርት ጉዳይ የራስ ፍላጎት በእጅጉ ወሳኝ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ውጤታማ ለመሆንም የመንፈስ ጥንካሬ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

ሴቶች ወደ ትምህርት ሄደው እንዲማሩ ለሚያውቋቸውና በዙርያቸው ላሉ ለአንዳንድ ወዳጅ ጓደኞቻቸው ምክር እና ድጋፍ ይሰጡ እንደነበር ወይዘሮ ምንትዋብ በአንድ ወቅት ተናግረው ነበር።

ከረዥም ጊዜ በፊት በኢትዮጵያ ሴት ሆኖ በአርክቴክት የሙያ መስክ ተሰማርቶ መስራት ብዙ ፈተና የነበረው እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ ምንትዋብ፤ የበታች ሰራተኛ በሚያዙበት ወቅት እንኳ ሴት አዘዘችኝ በማለት ግንዛቤው ስላልነበር ብዙዎች ይቆጡ እንደነበር ይናገራሉ፡፡ የዚህ መነሻም ሴት በቤት ውስጥ ብቻ አገልግሎት የምትሰጥ በወንድ ፍቃድ ስር የቆየች መሆኑ ያመጣው ችግር ነው ይላሉ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በኢትዮጵያ በብዙ መልኩ ከሌሎች የዓለም ሀገራት ባልተናነሰ ሁኔታ የሴትና የወንድ ዕኩልነት እንዳለም ወይዘሮ ምንትዋብ ይገልፃሉ።

ወይዘሮ ምንትዋብ በአንድ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ዕድገትን እንዴት ያዩታል ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፤ አዲስ አበባ በፍጥነት እየተለወጠች ያለች ከተማ ናት፤ ብዙ መንገዶች ተሰርተዋል። ዕድገትና የሚታይ ለውጥ አለ፤ ከተማዋ ውብ እየሆነች ነው። ለአንድ ከተማ የሚያስፈልገው መሰረታዊ ነገር መንገድ ነው። ከዚህ አንፃር አዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚታየው ለውጥ አስደሳች እንደሆነ ገልፀው ነበር።

የአዲስ አበባ ከተማ የበለጠ ጥሩ ገፅታ እንዲኖራት ደግሞ የሚሰሩ ስራዎች በተለይ የሕንፃ ዲዛይኑ ዕውቀት ባላቸው ሰዎች መሰራት እንዳለበት የሚናገሩት አርክቴክት ምንትዋብ አዱኛ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የሕንፃ ዲዛይን እንዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ እንደምገባ ተናግረው ነበር። ከዚህ ውጭ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ክልሎችን የማየት ዕድል እንደነበራቸው በመንገድ መሰረታ ልማት ተስፋ ሰጪ ለውጥ እንዳለ ይገልፃሉ።

ለከተማ ዕድገት ጥናት አስፈላጊ እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ ምንትዋብ፤ የባለሙያዎች ጥናትና ውይይት በጣም አስፈላጊ ነው። የሕንፃ ዲዛይን ሥራ ከስሜት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በጥሩ ስሜት የተሰሩት የድሮ የሕንፃ ዲዛይኖች ናቸው። አሁን የሕዝቡን ፍላጎት ለማሟላት ሲባል በፍጥነት የሚሰሩ ስላሉ ከአርክቴክቸራል ውበት አንፃር ሲታይ ብዙ የሚጎላቸው ነገር እንዳለ ያነሳሉ።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሕንፃ ጥንካሬውና ውበቱ ለከተማዋ ጥሩ ገፅታ ሰጥቷል የሚሉት ወይዘሮ ምንትዋብ፤ በተጨማሪም የብሔራዊ ትያትር እና የብሔራዊ ባንክ የሕንፃ ዲዛይኖች ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት የሚያላብሱ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በከተማዋ ድሮ የተሰሩ ሕንፃዎች የውጭ ሀገራት አርክቴክቶች እጅ ስላለባቸው ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር እንኳ በንፅፅር ሲቀርቡ የተሻሉ እንደሆነ ተናግረው ነበር።

የአዲስ አበባን የአየር ጠባይ ለመጠበቅ ተፈጥሮን ብዙ ሳንቃወም ዛፍ መትከልን እንደ ባህል መውሰድ የሚሉት ወይዘሮ ምንትዋብ፤ አሁን ያለውን ችግር ለማስወገድ ከሕዝቡ ጋር መመካከር ሕዝብን ማስተማር ያስፈልጋል። ሁሉም ዜጋ ለንፅህና መጠንቀቅና የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓቱን መስተካከል እንዳለበት በተደጋጋሚ ይናገሩ ነበር።

የመጀመሪያዋ ሴት አርክቴክት ምንትዋብ አዱኛ ካደጉበት ሀገርና ከተማሩበት ከሰሩበት የተለያየ ሀገር የተነሣ የአማርኛ፣ የኦሮምኛ እና የሶማሊኛ ቋንቋዎችን ከሀገር ውስጥ ከውጭ ደግሞ የእንግሊዘኛ፣ የጀርመንኛ እና የቡልጋሪያ ቋንቋን አቀላጥፈው መናገር የሚችሉ የስድስት ቋንቋ አዋቂ ነበሩ።

አርክቴክት ምንትዋብ አዱኛ የጡረታ ዕድሜያቸውን ከሴት ልጃቸው ጋር ኖረው፤ በክብር በተወለዱ በሰማንያ አምስት ዓመታቸው በዕለተ ሰኞ መስከረም 14 ቀን 2016 ዓ ም አርፈዋል። አርክቴክት ምንትዋብ የአንዲት ሴትና የአንድ ወንድ ልጆች እናት፥ የአራት ወንድ ልጆች አያት ነበሩ።

ስርዓተ ቀብራቸውም ማክሰኞ መስከረም 15 ቀን 2016 ዓ ም በመንበረ ጸባኦት ቅስድስ ሥላሴ ካቴድራል ቤተክርስቲያን ቤተሰብ፣ ዘመድና ወዳጆቻቸው በተገኙበት ተፈፅሟል። እኛም ለእኚህ ለብዙ ኢትዮጵያውያን ብሎም አፍሪካውያንና ለመላው ጥቁር ሴቶች ምሳሌ ለሆኑ ሀገራቸውንም በሙያቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ላስጠሩ የሀገር ዋርካ ዕንቁ ሴት ነፍስ ይማር እንላለን።

*** ለዚህ ፅሁፍ በ2004 ዓ.ም የታተመውን እምርታ መፅሔት እንደ ምንጭ ተጠቅመናል።**

# ስፖርት





## የወርልድ ቴኳንዶ ክለቦችን ለማቋቋም መመሪያ እየተዘጋጀ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

በኢትዮጵያ ወርልድ ቴኳንዶ ስፖርት ክለቦችን ለማቋቋም መመርያ አዘጋጅቶ ለማጽደቅ እየሰራ ይገኛል፡፡ የፓራ ቴኳንዶ ስፖርትን መልሶ ለመጀመር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የኢትዮጵያ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡

በኢትዮጵያ ተዘውታሪ ከሆኑ ስፖርቶች መካከል ወርልድ ቴኳንዶ ስፖርት አንዱ ቢሆንም፤ ክለቦች ግን በብዛት የሉም፡፡ በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በወርልድ ቴኳንዶ ስልጠናቸውን ተከታትለው የሚመረቁ ወጣቶች ክለብ ባለማግኘት ሲቸገሩ ቆይተዋል። ምንም እንኳን ሰልጣኞች በተገቢ ሁኔታ ስልጠናቸውን በማጠናቀቅ ብሔራዊ ቡድንን እስከመወከል ቢደርሱም የተወሰኑት ግን ባክነው ይቀራሉ፡፡ ለሰልጣኞች ብክነትና በስፖርቱ ብቁና ተወዳዳሪ ባለሙያዎች ላለመፍራቱ ዋነኛው ምክንያትም የክለቦች አለመኖር መሆኑ ፌዴሬሽኑ ያምናል፡፡ ነገር ግን ክለቦችን ለመመስረት በቅድሚያ መከናወን ያለባቸው ጉዳዮች ባለመሟላታቸው ሊሳካ አልቻለም፡፡ ክለብ ለመመስረት ፍላጎት ያላቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቢኖሩም ፌዴሬሽኑ በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት ክለብ እንዲያቋቁሙ ቢጠበቅም፤ በሚፈልገው ልክ እየተሰራ ባለመሆኑ ለየት ያለ መመርያ ማዘጋጀቱን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል፡፡

በ2016 ዓ.ም የፓራ ቴኳንዶ ስፖርትን መልሶ ለመጀመር በፌዴሬሽኑ የታቀደ ሲሆን፤ በዓመቱ የአካል ጉዳተኞች የቴኳንዶ ውድድር የሚካሄድ በመሆኑ ከዚህ በፊት በስፖርቱ ውስጥ የነበሩትን እና በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች በማሰባሰብ ስልጠና የሚሰጣቸው መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ የአካል ጉዳተኞች የቴኳንዶ ውድድር ከዚህ በፊት ተጀምሮ ሲቋረጥ መልሶ ለመጀመር እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም 12 የሚደርሱ የፓራ ቴኳንዶ ስፖርተኞች ተመርጠው በቅርብ ጊዜ በአንድ ቦታ የሚሰባሰቡም ይሆናል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለፓራሊምፒክ ስፖርት የሚደረገው ድጋፍ ከፍተኛ በመሆኑ በውድድሮች ለመሳተፍ መታቀዱንም ፌዴሬሽኑ አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍቅሩ ተቋም፣ ከክለቦች ምስረታ ጋር የተያያዘውን ጉዳይ ያብራራሉ፡፡ «ትልቁና እስከ ዛሬ መሰራት የነበረበት ክለብን የማቋቋም ጉዳይ ነው፡፡ ስልጠና ተመጋጋቢ በመሆኑ ታዳጊዎች አካዳሚ ገብተው ስልጠናቸውን አጠናቀው ከሚወጡት የተወሰኑት ብሔራዊ ቡድንን የሚቀላቀሉ ናቸው፡፡ ክለቦች ባለመኖራቸውም ለብሔራዊ ቡድን የተመረጡትን ጨምሮ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይበተናሉ፡፡ ክለብ ቢኖር ግን እነዚህን አቅፎ የሚይዝ ይሆናል፡፡ ከአካዳሚ የሚመረቁ ስፖርተኞችም የክለብ ተጫዋቾች በመሆን ተጠቃሚ ይሆናሉም» ብለዋል። ክለቦች ሲመሰረቱ የክለብ መስፈርትን በማሟላት ደመወዝ መክፈልን ጨምሮ በሁሉም ውድድሮች ስለሚሳተፉ የክለብነት ስያሜን ያገኛሉ፡፡ ለዚህም ለየት ያለና ስፖርተኛውንም ሆነ አሰልጣኙን የሚጠቅም እና ስፖርቱን የሚያሳድግ የቴኳንዶ መመሪያ በመዘጋጀት ሂደት ላይ እንደሆነም ተረጋግጧል፡፡

የክለቦች መመሪያ ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በተያዘው ወር መጨረሻ በሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ ክልሎች በመመሪያው መሰረት ክለብ እንዲመሰርቱ እንደሚያደርግም ኃላፊው ተናግረዋል። በዚህም ውስጥ ለውስጥ ንግግሮች እንዳሉና ክለቦችን ለመመስረት እቅድ ያቀዱ ተቋማትም አሉ፡፡ መከላከያ፣ ፌደራል ፖሊስ፣ የክልል ፖሊስ ተቋማትና ባንኮችም ክለብ ለመመስረት እቅድ ካላቸው ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚም ጉዳዩን ከክልሎች ጋር በመሆን መሰረት ለማስያዝ የመጀመሪያ እቅድ አድርጎ ይዟል፡፡ እስከ አሁን መሰራት ኖሮበት ባለመሰራቱ በተያዘው ዓመት የፌዴሬሽኑ የመጀመሪያ ስራው ክለብ መመስረትም ይሆናል፡፡ እስካሁን መዘግየቱም የወርልድ ቴኳንዶ ስፖርት መመሪያና ደንብ ባለመኖሩ ምክንያት ነው፡፡ መመሪያው በዓለም አቀፍ ደንብና ልምድ መሰረት ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ በመሆኑ በቀጣይ ጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ ተግባራዊም ይሆናል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የሚዲያ ሽፋን ለማግኘት ከዲኤስ ቲቪ ጋር ስምምነት እያደረገ ሲሆን፤ ለዚህም ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል።

ፌዴሬሽኑ ክለቦችን ከማቋቋም ባለፈ በ2015 ዓ.ም ታቅደው ያልተሰሩ ስራዎችን ከ2016 ዓ.ም እቅዶች ጋር አጣምሮ ማቀዱንም ጠቁሟል፡፡ የአቅም ግንባታ ስልጠናን ጨምሮ አብዛኞቹን እቅዶች ማሳካቱን አስታውቋል፡፡ የአሰልጣኝነት፣ የዳን ፕሮሞሽንና የዳኝነት ስልጠናዎችንም በሁሉም ክልልና ከተማ አስተዳደር መስጠትም ችሏል። በተጨማሪም አምስት የአፍሪካ ሀገራት የተሳተፉበት ዓለም አቀፍ የዳኝነት ስልጠና በሀገር ውስጥ አዘጋጅቶ ሊሰጥ ችሏል፡፡ ኢትዮጵያም አዘጋጅ በመሆኗ ከአርባ በላይ ዳኞች ተሳትፈውበታል፤ ከ40 ዳኞች 33ቱ ምዘናውን በማለፍ ዓለም አቀፍ ዳኞች መሆናቸው ታውቋል፡፡

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ፋሩቅ ዲኖ ሐሰን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-53805 የተሽከርካሪው አይነት ልዩ ጎታች የሻሲ ቁጥር LZFF25T44CD242462 ሞዴል KS3240 የሞተር ቁጥር F2CE0681B.B052.12CO0027714** የሊብሬ ቁጥር 0286206
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ክብሮም ገ/እግዚአብሄር ወ/ተንሳይ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-13228 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻሲ ቁጥር 437776 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር E0113711 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 28/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፍቃዱ ሀይሉ ቦጋለ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A89331 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻሲ ቁጥር JTB31PJ75X5001578 ሞዴል HZJ75LP-MRV የሞተር ቁጥር 1HZ-0283408 የሊብሬ ቁጥር 178473 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል።
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አንተሁን የሓላ ታፈረ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-83470 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር WJME3TRE6GC334519 ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር F3BEE681*B220-243777* የሊብሬ ቁጥር 0161729
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የኋላ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አነ መቅደስ በዛ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-82321 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር JSAETD01V00131583 ሞዴል ETD01V የሞተር ቁጥር G16B-538016 የሊብሬ ቁጥር 173805
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል።
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አበባው ሉሌ መኮንን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-79390 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር LZZ5BL5F1FN084179 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615.47*150807019247* የሊብሬ ቁጥር 0131625 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የን/ስ/ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዳዊት ኡርጌሳ ጉራራ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B34375 የተሽከርካሪ ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻሲ ቁጥር LKHNF1CH4DAU01546 ሞዴል HFJ1021GBE4 የሞተር ቁጥር DA465Q-1A2901252 የሊብሬ ቁጥር 321376 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 22/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዶ/ር ሐናን አብዱራህማን ኸይሩ ጅላሉ የሰሌዳ ቁጥር አ-አ 02-01-B29437 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር JTDBW23E620049992 ሞዴል NZE120L-AEPDKV የሞተር ቁጥር 2NZ-3512296 የሊብሬ ቁጥር 021727
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ብራስ ቢቨሬጅ ኤክስፐሬስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-61865 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JAAKP34HXB7P00289 ሞዴል NPR71 የሞተር ቁጥር 4HG1-837361 የሊብሬ ቁጥር 106370 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 2/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ቶማስ በቀለ አገቶ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C03456 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር MBHCZF63S00117930 ሞዴል CZF63S የሞተር ቁጥር K12MP-4225793 የሊብሬ ቁጥር 426318
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 3/2/2016 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ናትናኤል ሽፈራው ጉዳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-03779 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻሲ ቁጥር JT1WYH61V-00059836 ሞዴል HYES YH614 የሞተር ቁጥር 3Y-0428866 የሊብሬ ቁጥር 497206/055303/416539
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዳንኤል ደሬሳ ደገፋ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A00975የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JAAKP34H6E7P04697 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-165501 የሊብሬ ቁጥር 344542 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2016 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**